## ምዕርፍ 5

## 5. የአልጀርስ ስምምነት ኢ-ፍትሐዊነት ሲገመገም

እ.አ.አ በ2000 ዓ.ም በኢትዮጵያና በኤርትር መሃከል የተካሄደው ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት ከተደመደመ በኋላ የኤርትራ ወራሪ ጦር ከኢትዮጵያ ሲባረር የኢትዮጵያ ጦር በክትትል መጠነ ሰፊ ከሆነ ኤርትራ ግዛት ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ወታደራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎችን ይዞ መቆየት ሲችልና ኤርትራንም አንዳንድ ግዴታዎች ውስጥ ሳያስገባት በሩጫ እንዲወጣ የታዘበበት ምክንያት እስከ ዛሬም ምስጢር ሆኖ ቆይቶአል። ሆኖም ምናልባት ውስጠ ምስጢሩን ግልጥልጥ አድርጐ ሊያወጣው ባይችልም ቀደም ሲል ሕወሓት አመራር ውስጥ የነበሩና በአሁኑ ወቅት ደግሞ የዓረና ትግራይ ፓርቲ አመራርና የመድረክ አባል ወይዘሮ አረጋሽ አዳነ <u>አውራምባ ታይምስ</u> በሰጡት አስተያየት አንድ ጠቋሚ ነገር ሰንዝረዋል። እሳቸው እንዳሉት፣ “ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ፊት እየገሰገሰ በነበረበት ጊዜ ጦርነቱ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ይቆማል ብለው በሚድያ (በመገናኛ ብዙሃን) በማወጃቸው ነው ሠራዊታችን ወደ ኋላ እንዲመለስና የሻቢያ ሠራዊት ከሞትና ከመቃብር እንዲድን የሆነው”[112]።

ከዚያም የኢትዮጵያ መንግሥትም እንደዚሁ በአስቸኳይ አልጀርስ ሄዶ የወሰን መካለል ስምምነቱን መፈረሙ ለወሰን መካለሉ መሠረት ኢትዮጵያና ጣልያን በ1900፣በ1902 እና በ1908 ዓ.ም የተፈራረሙአቸው የቅኝ ግዛት ውሎች አግባብነት ያላቸው አለም አቀፍ ሕጐችና እንዲሁም የአፍሪቃ

[112] ወይዘሮ አረጋሽ አዳነ <u>አውራምባ ታይምስ</u>, ቅዳሜ ሚያዝያ 1 ቀን 2003 ዓ.ም



ከዚህ በላይ ቢገለጽም ለማስታወስ ያህል እዚህ ላይ እንደገና ማንሳት አስፈለገ።

የመካለሉ ውሳኔ በእነዚህ ውሎች፣ በዓለም አቀፍ ሕግና በአፍሪቃ አንድነት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ በውሳኔው ወቅት ፍትሐዊነት ርዕታዊነት ወይንም አዘኔታ ወይንም አመክንዮት የመሳሰሉ ለፍትሐዊነት ግብአት ሊሆኑ ይችሉ የነበሩ ነገሮች ሁሉ (ex aequa et bono) ከእሳቤ እንዳይገቡ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተው አምስት አባላት የሚገኙበት የድምበር ኮሚሽን ሆላንድ ዘሔግ ውስጥ ተቋቋመ።

### 5.1. ተዋዋዮቹ

አንድ የአገር ሉዐላዊነት የሚነካ ይሁን ተራ የበሬ ሽያጭ ውል ቢያንስ በሁለት ወይንም ከዚያ በበለጡ ውል የመዋዋል ችሎታ ወይንም ሕጋዊ ብቃት (Legal capacity) ባላቸው ሰዎች ወይንም አካላት መሃከል መፈጸም ይኖርበታል። ውሉም የሚያስረው በሌላ መልኩ ካለተገለጸ በስተቀር ተዋዋዮቹን ወይንም በሕግ የወከሉትን ብቻ ሲሆን ሌላ ሰው ወይንም አካል ባልተደራደረበትና ባልተስማማበት ውል ሊጠቀምም ሆነ ሊጠየቅ አይችልም።

ኢትዮጵያና ጣልያን የፈረሙአቸው ውሎች እንደውልነታቸው ብዙ ማሟላት የነበረባቸው ሕጋዊ ሁኔታዎች ቢኖሩም ለጊዜውም ቢሆንም ሕጋዊ ውሎች ናቸው ብለን ብንቀበላቸውም እንኳን አሳሪነታቸው ተዋዋዮቹን ጣልያንና ኢትዮጵያን እንጂ በውሉ ውስጥ ያልነበረችው ኤርትራን አይመለከትም ውሎቹ በተፈረሙበት ጊዜ ኤርትራ የጣልያን ቅኝ ግዛት ስለነበረች ውል ለመዋዋል የሚያስችል ሕጋዊ ሰውነት አልነበራትም።

እዚህ ላይ በጊዜው ኤርትራ የጣልያን ቅኝ ግዛት ስለነበረች ጣልያን ከኢትዮጵያ ጋር የገባችው ግዴታም ሆነ መብት ኤርትራ ነፃ ስትወጣ ወርሳለች ወይ የሚል ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። አንድ አገር ከቅኝ ግዛት ነፃ ሲወጣ ቅኝ ገዢው የገባቸው ግዴታዎችን እንደገና ተደራድሮ ግዴታውን ካላደሰ ቅኝ ገዢው ከገባው ግዴታ አዲሱ አገር ነፃ መሆኑን ወይንም እንደማይመለከተው ስለአገራት

የተቀበሉት የ1978 ዓ.ም የቪየና ኮንቬንሽን አንቀጽ 16 ይደነግጋል[113]::

ይህንኑ በማረጋገጥ አምባሳደር ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ በቅኝ ገዢዎች ቀድሞ ይተዳደር የነበረ ግዛት ለአዲሱ መንግሥት ሲተላለፍ አዲስ ኢንተርናሽናል ሕይወት መጀመሩ ስለሆነ ከማናቸውም ግዳጅ ነፃ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባሉ::[114]

እንዲሁም የኔሬሬ ዶክትሪን የተባለው የሕግ መርሆ ቅኝ ግዛት የነበሩ አገራት ነፃ ሲወጡ የቅኝ ገዢዎቻቸው የገቡት ግዴታ አይወርሱም የሚል ሲሆን በቪየና ኮንቬንሽንም ሆነ በኔሬሬ ዶክትሪን መሠረት ቅኝ ገዢዎች የገቡባቸው ግዴታዎች በአዲሱ አገር ላይ አሳሪ የሚሆኑት አዲሱ አገር እንደገና ተደራድሮ አዲስ ግዴታ ውስጥ የገባ እንደሆነ ብቻ ነው[115]:: ስለሆነም በ1900 ዓ.ም. በ1902 ዓ.ም እና በ1908 ዓ.ም. ጣልያንና ኢትዮጵያ የተፈራረሙአቸው ውሎች በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል ለተፈጠረው ውዝግብ አግባብነት ስለሌላቸው ለድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት ሊሆኑ አይችሉም:: በእነዚህ ውሎች ተመርኩዞ የሚሰጥ ማንኛውም ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ውሳኔው በሕግ ፊት ዋጋ አይኖረውም::

## 5.2. የተዋዋዮች አቀም አለመመጣጠንና ኢትዮጵያ በውሉ ለሰጠችው ምንም አለማግኘቷ

ጣሊያንና ኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሱ ውሎችን በፈረሙ ጊዜ በኢኮኖሚ አቅም፤ በወታደርና ትጥቅ ዝግጅት፤ እንዲሁም በየአገራቱ ላይ ሊያሳርፉ የሚችሉት የዲኘሎማሲ ጫና የሚመጣጠኑ አልነበሩም:: ውሎቹ በተፈረሙ ጊዜ ጣልያን በኢኮኖሚ የዳበረች፤ በጦር ኃይሏ የጠነከረች ዘመናዊ አገር ስትሆን

---

[113] Vienna Convention on Succession of States in Respect of Treaties, 1978.
[114] ኃይሉ ወልደጊዮርጊስ (አምባሰደር) ሰለአባይ ውሃ ሙግት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኘሬስ, (2001 ገጽ 191.

[115] Vienna Convention on Succession of States, supra note.113.



ስትሆን ኢትዮጵያ ደግሞ ደካማና ድሀ እንደ መሆንዋ መጠን የሁለቱ አገራት ኃይል የተመጣጠነ ነበር ለማለት ካለመቻሉ ሌላ ጣልያንና ሌሎችም የአውሮፖ አገራት ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ የሚጥሩበት ጊዜ ነበር:: የኢትዮጵያ በሁሉም መስክ ደካም ሁኔታ ላይ ሆና ከጣልያን ጋር የገባችው ውል ዋጋ ቢስ ነው::ሁለቱ ተዋዋዮች ኢትዮጵያና ጣልያን በምንም መልኩ የሚመጣጠን ኃይልና አቅም አልነበራቸውም:: ውሉች ሙሉ በሙሉ ወደ አንድ ወገን ያጋደሉ ከመሆናቸውም በላይ ኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛቶችዋን ስታስረክብ በለውጡ ምንም ያገኙችው ነገር ስለሌለ ሕጋዊ ውሉች ነበሩ ለማለት አይቻልም::

## 5.3. ኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛቶችዋን እንድታስርክብ ተገድዳ የፋረመቻቸው ውሉች

ጣልያንና ኢትዮጵያ እነዚህን ውሎች በተፈራረሙበት ወቅት የአውሮፖ ቅኝ ገዢዎች አፍሪቃን በቅኝ ግዛትነት ለመቀራመት ከፍተኛ ትንቅንቅ ውስጥ የገቡበት ጊዜ ነበር:: አጼ ምኒልክ የመጀመርያውን ማለት የ1900 ዓ.ም. ሰነድ የተጫነባችው (ፈርመውት አያውቁም) አውሮፖውያን በጀርመን ዋና ከተማ በበርሊን ተገኝተው አፍሪቃን እንደ ቅርጫ ሥጋ ከተቀራመቱበት ከሁለት ዓመታት በኋላ ነበር:: በዚህ ሸሚያ አንዷም አገር ያልደረሳት ጣልያን ብቸኛዋ ነፃ አፍሪካዊት አገርን ኢትዮጵያን ለመዋጥ ወስና ለዚሁ ግብ እንግሊዝና ፈረንሳይ ሲደግፉአት ቆይተው ነበር::

ስለሆነም ኢትዮጵያ በሰሜኑ በኩል በጣልያን፣ በምሥራቅ አሁንም በጣልያን በፈረንሳይና በእንግሊዝ፣ በደቡብ አሁንም በእንግሊዝ፣ በምዕራብ አንደገና በእንግሊዝ ተከብባ ጭንቅ ውስጥ የነበረችበት ጊዜ እንደነበር ቀደም ሲል ተገልጻአል:: እነዚህ ኃይሎች በተለያዩ ጊዜአት የኢትዮጵያን ወሰን ጥሰው በመግባት ጉዳት ያደርሱ ነበር:: የወልወሉ ትንኮሳ ዋነኛው ምሳሌ ሲሆን በሌሎችም አካባቢዎች ተመሳሳይ ጥቃቶች ይሰነዝሩ ነበር::

አጼ ምኒልክ እነዚህን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ግዛቶችን አሳልፈው የሚሰጡ ውሎች የፈረሙት በነበረባቸው ጫና ምክንያት ተገድደው

ተገድደው ለመሆኑ አያጠራጥርም። ኢትዮጵያም በጦር ኃይል፣ በኢኮኖሚና በዲፕሎማሲው በክብራባት ድክመት የጣልያንና የሌሎች የአውሮፓ አገራት ጫና ለመቋቋም የሚያስችል አቅም አልነበራትም። አንድ ተዋዋይ ውል እንዲገባ ወይንም ስምምነት እንዲፈርም ማስገደድ ሕገ ወጥ እንደመሆኑ መጠን እንዲህ ዓይነቱ ስምምነት ከመነሻው በሕግ ፊት ዋጋ አይኖረውም[116]።

አጼ ምኒልክ ተገድደው ባይሆን ኖሮ የኢትዮጵያ የጥንት ግዛቶችን ወደ ጣለያን የሚያጥፉ ውሎችን በምንም ዓይነት ባልተቀበሉም ነበር። ማንም በተለይም እንደ አጼ ምኒልክ ያለ አገር ወዳድና የአገር አባት ተገድዶ ካልሆነ በስተቀር የአገሩን ታሪካዊ ክፍሎች ቆርጦ ለጠላት ሰጥቶ የባህር በርን የሚዘጋ ውል አይፈርምም።

በማስገደድ ወይንም በማስፈራራት የሚፈረም ውል ፍርስ ስለሆነ በተዋዋዮቹ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም። በማንኛውም አገር የውል ሕግም ሆነ በዓለም አቀፍ የውል ሕጐች እንዲህ ዓይነት ውል ፍርስ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ 1 9 9 4 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት የተደነገገው የውል ሕግ አንቀጽ 3 9 አንድ ተዋዋይ ውል ውስጥ እንዲገባ ማስፈራራት የተደረገበት ከሆነና ይህም የተደረገበት ማስፈራራት ሊቋቋመው የማይችል ከሆነ ውሉ ፍርስ ነው ይላል[117]።

በተጨማሪም እ.አ.አ በግንቦት 2 2 ቀን 1 9 6 9 ዓ.ም. የውል ሕጐችን አስመልክቶ በተደነገገው የቪዬና ስምምነት (V i e n n a C o n v e n t i o n) አንቀጽ 5 2 በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የተጠቀሱትን መርሆችን በመጣስ፣ ወይንም በማስፈራራት ወይንም በማስገደድ የተደረገ ውል ዋጋ እንደሌለው ይገልጻል[118]።

በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ከተጠቀሱት መርሆዎች አንዱ የአገራት ሉዓላዊነት በሌላው አለመደፈር ሲሆን ጣልያኖች ግን የኢትዮጵያ የጥንት ግዛቶችዋን በመጠቅለል በኢትየጵያ ሉዐላዊነት ላይ በደል ፈጽመዋል ። በተጨማሪም ኢትዮጵያ

---

[116] Id

[117] Id

[118] Id



ውሎቹን ስተፈርምና ግዛትዋን ስትለቅ ከላይ እንደተገለጸው በለውጡ ያገኘችው ጥቅም የለም። ስለሆነም በዚሁ በቪዬና ኮንቬንሽን መሠረት ውሎቹ አሁንም ፍርስ ናችው።

የቪዬና ኮንቬንሽን ሕግ ሆኖ የወጣው ውሎቹ ከተፈረሙ በኋላ ቢሆንም አንድ ሕግ ደግሞ አሳሪነት የሚኖረው ሕጉ ከወጣበት ወይንም ከታወጀበት ጊዜ በኋላ ለሚፈጸሙ ድርጊቶች ብቻ እንጂ ሕጉ ወደ ኋላ ሄዶ እንዳይሠራ መደንገግ መሠረታዊ የሕግ መርህ ነው። ይህ የቪዬና ኮንቬንሽን የሚደነግገው ቀደም ሲል ይታወቁ የነበሩት ዓለም አቀፍ ልማዳዊ ሕጐችን (Customary International Law) ስለሆኑ በእነዚህ በአጼ ምኒልክና በጣልያኖች በተፈረሙ "ውሎች" ላይም ተፈጻሚነት አላቸው። ይህ አቋም ከላይ ለተጠቀሰው በ1994 ዓ.ም ለተደነገገው ለተባበሩት መንግሥታት የውል ሕግም አግባብነት አለው።

ስለሆነም እነዚህ በኢትዮጵያና በጣልያን መሃከል የተፈረሙ ሦስቱም ውሎች በእነዚህ በተለያዩ ሕጐች መሠረት ፍርስ ስለሆኑ ለድንበር መካለሉ ሊያገለግሉ አይችሉም። በእነዚህ ሕገ ወጥ ውሎች በመመስረት የተሰጠ ውሳኔም ዋጋ ቢስ ነው።

አምባሳደር ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ሱዳንና ግብጽ ለጥቅማቸው ምቹ ያልሆኑ የቅኝ ግዛት ስምምነቶችን ውድቅ እንዳደረጉ ሁሉ ኢትዮጵያም አባይን አስመልክቶ ተመሳሳይ አቋም መያዝ ምንም የሚከለክላት ነገር እንደሌለ ከገለጹ በኋላ ፍስሐ ይመር (አምባሳደር) የተባሉ የሕግ ባለሙያ ይህንኑ አቋም በአንድ በኖሩት መጣጥፍ እንደሚደግፉ ጠቁመዋል።

በአልጀርስ የድምበር ኮሚሽን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያዊ መንግሥት ተባባሪ ተወካይ (ሌላው አቶ ሥዩም መሥፍን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሲሆኑ) አምባሳደር ፍስሐ ይመር የሱዳንና የግብጽ የቅኝ ግዛት ውሎችን ውድቅ መሆናችው ሲደግፉ እንዴት ብለው ነው በኢትዮጵያ ላይ ሲሆን የቅኝ ግዛት ውሎች አሳሪና ዋጋ አላቸው በማለት ለድርድሩ መሠረት እንዲሆኑ የተስማሙት?

ኢትዮጵያ የፋረመቻችው የቅኝ ግዛት ውሎች ከመሠረቱ እንደ ውልነታቸው ችግር ደባባቸው ስለሆኑ በውን በሕግ ፊት የተሟሉ ውሎች ናቸው ሊባሉ አይችሉም፡፡

## 5.4. የውሎቹ ጉድለቶችና ውድቅ መሆናቸው፡፡

የድምበር ኮሚሽኑ ውሎች ለውሳኔው መሠረት ካደረጋቸው አንዱ የ1900 ዓ.ም "ውል" እንግሊዝና ጣልያን የተፈራረሙበት ስምምነት ሲሆን ሁለቱ አገራት ከሰቲት እስከ መተማ ያለውን ወሰን ወደ ምሥራቅ በማካለል ከጎንደር ወደ ኤርትራ የሚወስደው የንግድ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ እንዲታጠፍ ያደርጋል ይላል፡፡ ለዚህም ለኢትዮጵያ ለተሰጠው ሰፊ መሬት ልዋጭ የኩናማ ጎሳ በሙሉ እስከ መረብ ድረስ ለኤርትራ (ለጣልያን) ኢትዮጵያ እንድትለቅ የእንግሊዝና የጣልያን ወኪሎች አጼ ምኒልክን እንዲጠየቁ ይወስናሉ፡፡ የኢትዮጵያ ስምምነት እስኪገኝ ድረስ በስምምነቱ የተወሰነው ሁሉ ምስጢር ሆኖ እንዲቆይ እንግሊዝና ጣልያን ተስማሙ[119]፡፡

ይህ ሰነድ ለአጼ ምኒልክ ወይንም ለወኪሎቻቸው ቀርቦ አልተፈረመበትም፡፡ ወይንም በሌላ መልኩ ኢትዮጵያ ይህንን ውል ፊርማ የተቀበለችበት ጊዜ የለም፡፡ ማንኛውም የውል ረቂቅ ዋጋ እንዲኖራው ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ወይንም አካላት መፈረም ይኖርበታል፡፡ ከተፈራረሙም በኋላ የየአገሩ ሕግ በሚደነግገው መሠረት በንጉሡ ወይንም በፖርላማው ወይንም በሌላ ውል ለማጽደቅ ሥልጣን በተሰጠው አካል መጽደቅ ይኖርበታል፡፡ ከላይ የተጠቀሰው እንግሊዝና ጣልያን የተፈራረሙት ሰነድ ኢትዮጵያን ሊያስር የሚችል የተሟላ ውል አይደለም፡፡ ይህ አቋም በዚህ ጉዳይ ምርምር ያዳረጉ በጄኔራል አበበ ተክለ ሃይማኖት ካህሣይና በአቶ ምገስ ስለምን የተደገፈ ነው፡፡ በጄኔራሉ አስተሳሰብ ሰነዱ ውል ሳይሆን ሁለቱ ወገኖች የተለዋወጡት ማስታወሻ ተደርጎ መታየት አለበት[120]፡፡ በዚህ ጽሁፍ በተለያዩ ቦታዎች ይህ ሰነድ

[119] የኤርትራ ቅኝ ግዛት የህግ መጽሐፍ ከአራተኛው ጥራዝ ከገጽ 779-780 በጣልያንኛ የተጻፈው ፤1962 ዓ.ም

[120] Abebe T. Haimanot Kahsay. supra Note 3.



"ውል" እየተባለ ቢጠቀስም ሰነዱ "ውል" ነበር ለማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም የአልጀርስ የድምበር ኮሚሽን ውሳኔውን የሰጠው በሕግ ፊት በተሟሉ ውሎች ሳይሆን በተራ ማስታወሻ ነው ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ በኮሎኒያሊስቶች ተከብባ ጭንቅ ውስጥ በነበረችበት ጊዜያት የፈረመቻቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ለወሰን መካለሉ መሠረት እንዲሆኑ ኢሕአደግ ሲስማማ ምን አስቦ ነው የሚል ጥያቄ ጉዳዩን በሚያውቀው ሰው ሁሉ አእምሮ የሚጉላላ ጥያቄ ነው፡፡ ከአንዳንድ የቀድሞ ሕወሐት አባላት አካባቢዎች እንደተደመጠው ከሆነ ውሎቹ ለኢትዮጵያ ይበጃሉ፤ የኢትዮጵያን ጥቅም በሚገባ ያስጠብቃሉ ከሚለው ተነስተው እነደነበረ ይናገራሉ[121]፡፡

ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛትነት ቀንበር ልታሸክም ትራራጥ የነበረችው ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የጫነቻቸው የቅኝ ግዛት ውሎች እንዴት የኢትዮጵያን ጥቅም ሊያስጠብቁ ይችላሉ ተብሉ ይታሰባል? የኢትዮጵያ የጥንት የሰሜን ግዛቶችን የሚነጥቁ የባህር በሮችዋን የሚዘጉ ውሎች ኢትዮጵያን ሊጠቅሙ ይችላሉ ማለት "አይናችሁን ጨፍኑ እናሞኛችሁ" ከማለት አይዘልም፡፡ ቅኝ ገዢዋ ጣልያን የኢትዮጵያ ሥልጣኔ መሠረት የሆኑትን ግዛቶች ከኢትዮጵያ የነጠቀችውና ይህንን ትልቅ አገር ወደብ አልባ ያደረገችው ለእኛው ለኢትዮጵያውያን አስባና ተጨንቃ ነው እንደ ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያና ጣልያን የተፈራረሙአቸው የድንበር ውሎች አምስት ጊዜ ያህል ሞተዋል፤ተሰርዘዋል፡፡

- በተለያዩ ሕጋዊ ምክንያቶች ማለትም ውሎቹ በኢትዮጵያ ላይ በግድ በመጫናቸው፤ኢትዮጵያ፤ ሉዐላዊ ግዛቶችን ለጣልያን ለማስረከብ በመገድድዋ፤ በውሎቹ ተጠቃሚዋ ጣልያን ብቻ ሆና ኢትዮጵያ በልዋጩ ምንም ባለማግኘትዋ ውሎቹን ፍርስ ናቸው፡፡

[121] Ibid

- ጣልያን ከኢትዮጵያ ጋር የፈረመቻቸው ውሎችን በመጣስ ኢትዮጵያን ወርራ ከኢትዮጵያ ጋር የተስማማችባቸው ድንበሮችን አፍርሳ ኢትዮጵያ ኤርትራና የጣልያን ሶማልያን አንድ ላይ አጣምራ "የጣልያን ምሥራቅ አፍሪቃ ግዛት"(Italian East African Empire) በመመስረትዋ ውሎቹን አፍርሳቸለች።
- ሁለታኛው የዓለም ጦርነት ተደምድሞ ድል አድራጊ አገራትና ጣልያን ሌሎችም አገራትን ኢትዮጵያንም ጨምሮ በ1947 ዓ.ም በተፈራረሙት የሰላም ውል አንቀጽ 23 ጣልያን በአፍሪቃ የነበራት ማንኛውም መብቶች ሲሰረዙ ከኢትዮጵያ ጋር የተፈረርመአቸው ውሎቹም አብረው ተሰርዘዋል።
- እ.አ.አ በዲሴምበር 1952 ዓ.ም የተባባሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በውሳኔ ቁ.390 (V) ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን ስር በፌዴሬሽን ሲያስተሳስር ቀደም ሲል ጣልያንና ኢትዮጵያ የተፈራረሙአቸው ውሎች ተሰርዘዋል።
- እነዚህ ጣልያኖችና ኢትዮጵያ የተፋረረሙአችው ውሎች ኤርትራና ኢትዮጵያ እንደገና ተደራድረው አላደሱአቸውም። ስለሆነም እነዚህ ውሎች ምንም በማያጠረጥር መልኩ መሞታቸው እንኳን የሕግ ልሂቃንና የአገር መሪዎች ቀርቶ አንድ የአንደኛ ደርጃ ተማሪ እንኳን ሊረዳው የሚችል ነው።እጅግ በጣም የሚገርመው ደግሞ በአጼ ኃይል ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን እነዚህ ሦስት "ውሎች" በነጋሪት ጋዜጣ በወጣ ትዕዛዝ ቁጥር 6/1952 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተሰረዙ መሆኑን እያታወቀ ለአልጀርስ ስምምነት መሠረት መሆናቸውን ነው። "የመርዛም ዛፍ ፍሬ መርዛም ነው" በሚለው የሕግ ብሒል መሠረት ሕገ ወጥ ውሎች የአልጀርሰ ሕግ ወጥ ስምምነትና ውሳኔን ወልደዋል። ስለሆነም እነዚህ ውሎች ለድንብር መካለሉ መሠረት ሲሆኑ ውሎቹ መፍረሳቸው እነዚህ የሕግ ልሂቃንና የአገር መሪዎች አልተረዱም ማለት በፍጽም አይቻልም። ጉዳዩ የሌላ ነው ብሎ ለመደምደም ያስግድዳል ።

ኮሚሽኑ ለውሳኔው መሠረት ያደረጋቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ፍርስ መሆናቸው ከዚህ በላይ በሰፊው ተብራርቶአል። ሁለተኛው ለውሳኔው መሠረት የሆነው የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የመሪዎች



ጉባዔ በካይሮ ያሳለፈው ወሳኔ ቁ.AHG/Res/16/1 የአፍሪቃ አገርት ነፃ ሲወጡ የነበራቸው ወሰን ይከበር የሚለው መርህ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ የወሰን ማካለል አግባብነት እንደሌለው ከላይ ተጠቅሶአል። ይህ ውሳኔ ቃሉ እንደሚያስረዳው አግባብነት ያለው ቅኝ ግዛት ለነበሩ አገራት ነው። ከሕወሓትና ሻቢያ በስተቀር ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበርች ያለ ማንም አልነበርም። የአፍሪቃ አንድነት ድርጅትም ሆነ የተባበሩት መንግሥታት በጠቅላላው የዓለም ሕብርተሰብ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አድርገው አልቁጠሯትም። በተባበሩት መንግሥት ጸረ ኮሎኒ ኮሚቴም ሆነ በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ጸረ ኮሎኒ ኮሜቴ ኤርትራ እንደቅኝ ግዛት የተመዘገበችበት ጊዜ የለም። እንድ ፕሮፌሰር ንጉሤ አየለ አባባል "………የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት መቼም ቢሆን ሻቢያ በአፍሪቃ ውስጥ ትግል እንደሚያደርግ እንደ የነፃነት ታገይ ቡድን (Freedom fighting group) በመቁጠር እንደ ሌሎች ለነፃነት ታጋዮች" ድጋፍና እርዳታ አደርጎለት አያውቅም[122]። ስለሆነም የድምበር ኮሚሽኑ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አለመሆንዋ እየታወቀ ኮሚሽኑ ይህ የሕግ መርህ ለውሳኔው መሠረት ማድረጉ የሚገርም ከመሆኑም በላይ ግልጽና እውቆ የተደረገ ስህተት ነው።

## 5.5. የቅኝ ግዛት ውሎች ለወሰን መካለሉ መሠረት እንዲሆኑ የአሜሪካ መንግሥት የተጫወተው ሚና

እነዚህ የቅኝ ግዛት ውሎች ለወሰን መካለሉ መሠረት እንዲሆኑ የተመረጡት በቢል ክሊተን (Bill Clinton) አስተዳደር ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪቃ ጉዳይ ኦፊሰር በነበሩት በሱዛን ራይስ (Susan Rice) ግፊት እንደነበር በኢትዮጵያው የድርድር ቡድን ውስጥ ተመድበው የነበሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ተሰታፊ ለዚሁ ጸሐፊ ገልጸውለታል።

---

[122] ንጉሤ አየለ ፕሮፌሰር (የቀድሞ አምባሳደር)፤ "ያቀጋችን ቁራጭ መሬት አይደለችም" ሞኒልክ 15 ሐመሌ 1992 ዓ.ም ,

ኤርትራ ቀይ ባህርን በማዋሰንዋ ለመካከለኛው ምሥራቅና ለባብኤል መንደብ ባላት ቅርበት እጅግ ስትራተጂክ በሆነ አካባቢ የምትገኝ ስትሆን ይህንኑ በመገንዘብ አሜሪካኖች በአጼ ኃይለ ሥላሴ የአስተዳደር ዘመን አሥመራ አጠገብ የሚገኘው ቃኘው የተባለ የመገናኛና የስለላ ሰፈር አቋቁመው ነበር። አሜሪካኖች አሁንም ይህንን በጣም ስትራተጂክ የሆነችውን ኤርትራን በቁጥጥራቸው ስር ለማስገባት በብዙ ጌትነዋል። የኤርትራው ፕሬዚዳንት አቶ ኢሣያስን፣የኡጋንዳው ፕሬዚዳንት ዮዎሪ ሙሰቬኒን፣ የሩዋንዳው ፕሬዝዳንት ፖል ካጋሜንና፣ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ጨምሮ ቀይቶ ሲቆጫቸው "አዲሶቹ የአፍሪቃ ዴሞክራቲክ መሪዎች" እያሉ አሞካክሸአቸው ነበር። ከእነዚህም መሪዎች በተለይም ከኤርትራ ጋር ቅርበት ለመፍጠር በብዙ ጥርዋል፣ የዛሬዋ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሂላሪ ክሊንተን (Hillary Clinton) የአሜሪካ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ተደማጭ አባል በነበሩት ጊዜ ኢትዮጵያን ከጉዳይ ሳይጥፋ ኤርትራን ጎብኝተው ወደ ኢትዮጵያ ሳይዘልቁ ወደ አገራቸው መመለሳቸው የሚታወስ ነው።

ከላይ እንደተገለጸውም ደርግ በኢሕአደግና በሻቢያ ተሸንፎ ኢሕደግ አዲስ አበባ፣ ሻቢያ አሥመራ ለመግባት ጥቂት ቀናት ሲቀራቸው አሜሪካ ኢሕአዴግን፣ ሻቢያንና የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን (ኦነግ) በለንደን አሰባሰባ በማደራደር ኤርትራን በማዋለዱ ሂደት ከፍተኛ ሚና ተጫውታ ስለነበር ኤርትራን የራስዋ ፍጡር አድርጋ በመቁጠር በአንድ ወቅት "ኤርትራ የሹም ዶሮ ነች፣ ክፍ አትበልዋት" ወደ ማለቱ ደርሳ ነበር።

አሜሪካ የኤርትራን እጅግ ስትራቴጂካዊነት በመረዳት በቁጥጥሬ ስር አውላታለሁ በሚል እምነት ይመስላል ቀደም ሲል የአገራት ሉዐላዊነት አጥብቃ ትደግፍ የነበረችዋ አሜሪካ በተባበሩት መንግስታት መድርክ የተናገሬችውን በመለወጥ የኤርትራን መገንጠል በጽኑ ደግፍለች። በአፍሪቃ ቀንድ ሽብርኝነት ብቅ ብሎ ኢትዮጵያ እንደገና የአሜሪካ ጥብቅ ወዳጅ እስከሆነችበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ለአሜሪካ ጠቃሚነትዋ እጅግም ስላልነበረ ወደብ አልባዋን ኢትዮጵያን ትታ ድጋፍዋን ወደ ኤርትራ አዞረች። በአንድ ወቅት እንዲያውም ኢትዮጵያ በአካባቢው ካለ አገሮች በሦስትና በአራት እጅ ስለምትገዘፍ



ይህም ለአካባቢው ሰላምና ደህንነት አደገኛ ስለሆነ፣ ኢትዮጵያ ከአካባቢው አገሮች እኩልና ተመጣጣኝ እንድትሆን ወደ ሦስትና አራት ቦታ መከፋፈል አለባት የሚለው ሃሳብ ሲናፈስ ነበር። ይህን መሳይ አስተሳሰብ በሌሎች አካባቢም ይናፈቅ እንደነበር ፕሮፌሰር መስፍን ጽፋዋል

> *....አንዳንድ ኃያላን አገሮች አደዲስ አገሮች እንዲፈጠሩ ተጽእና እንዲሚያደርጉ በቅርቡ በአውሮፓም ሆነ በአፍሪቃ "ያልተሳካለቸው" አገሮች በእንግሊዝኛ "ፌይልድ ስቴትስ" በሚል አርዕስ ከአሜሪካ አንድ ሰነድ ወጥቶ ነበር ። ዓላማው እነዚህ ያልተሳካላቸው፣ የአፍሪቃ አገሮች በጉሣ ለመሸንሸንና ትናንሽ አገሮች ለመፍጠር ነበር። በዓላማው ከአፍሪቃ መሪዎች" ተሰማምተዋል ተብለው የተጠቀሱት ዚናዊው መለስ ናቸው*[123]

ስለዚህ አሜሪካ በቁጥጥርዋ ስር ለማስገባት ያሰበቻትን ኤርትራን ለመጥቀም ኢትዮጵያን የሚጎዱ ውሎች ለድንበር መካለሉ መሠረት እንዲሆኑ ጫና ብታደርግ አይገርምም።

የቅኝ ግዛት ውሎች ለድንበር መካለሉ መሠረት ይሁኑ ሲባል ኤርትራን ለመጥቀም መሆኑ የአንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሊረዳው የሚችለው ጉዳይ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት አገርን የሚያስቀማ፣ የባህር በርን የሚያዘጋ ሕገ ወጥ ውሎች ለድንበር መካለል መሠረት ይሁኑ ሲባል እሺ ብለው መቀበላቸው አንድም ስህተት ሲከፋም ክህደት ነበር ብሎ ከመፈረጅ አማራጭ የለም።

## 5.6. ፍትህና ዕርት ለድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት እንዳይሆን የተደረገ ገደብ

ኤርትራና ኢትዮጵያ በመሃከላቸው ያለውን ድንበር ለማካለል መሠረት ያደረጉአቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ፣አግባብነት ያላቸው የዓለም አቀፍ ሕግጋትና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የ1964 ዓ.ም የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ ብቻ መሆናቸው ይታወሳል። በማካለሉ ጊዜ የሚገጥሙ አንዳንድ ኢፍትሐዊ ሁኔታዎቹን ለማረም የሚያስችል ፍትሕ ርትዕ፣ሰብአዊ እርህራሄ (ex aequa et

[123] መስፍን ወልደ ማርያም፣ፕሮፌሰር፣ ቸር ከማሁ 3ኛ ገጽ 25

bono) ከግንዛቤ እንዳያገቡ ስምምነቱ ይከለክላል:: ስለሆነም ከነኚሁ ከተጠቀሱት ሕግጋትና መመርያ ውጭ በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ ምንም ዓይነት ችግር ቢፈጠር ኮሚሽኑ ለፍትሕና ለርትዕ ሲል አስተያየት አድርጎ ውሳኔውን ሊያርመው አይችልም:: ወሰኑ በሚካለልበት ጊዜ በቅኝ ግዛት ውሎችና በተጠቀሱት መመርያዎች መሠረት ብቻ ይሁን ሲባል የወሰኑ መስመር የሚያርፍባቸው በታዎች ምድረ በዳዎች ሳይሆኑ ለብዙ ዘመናት ሕዝብ የሰፈረባቸው በታዎች መሆናቸውን መዘንጋት አይገባውም ነበር:: የኢትዮጵያ ጠበቆች ወይንም ተወካዮች በምዕራቡ በኩል በአንደንድ በታዎች መስመሩ ትምህርት ቤትን፤ ቤተክርስቲያንና የመቃብር በታዎች ለሁለት ሊከፍል እንደሚችል ማወቅ ነበረባቸው::

እንደዚሁ ዓይነት ጉራማይሌ ሁኔታ በተፈጠሩ ጊዜያት የድንበር ኮሚሽኑ ይህንኑ የሕግ መርሆ (ex aequa et bono) ተከትሎ ፍትሕ ርትዕ ወይንም አመክንዮ ተጠቅሞ የድንበሩን ማስተካከል አይፈቀድለትም:: ይህ ሁኔታ የሚጎዳው ኢትዮጵያ ነው:: ምክንያቱም የድምበር ኮሚሽኑ ያስመረው የማካለል መስመር ከላይ እንደተጠቀሰው ቤተክርስቲያን ከመቃብር ቦታ ይልያል ተማሪ ቤትን ለሁለት ይከፍላል:: በስምምነቱ መሠረትም ኮሚሽኑ እነዚህን ውጥንቅጥ ሁኔታዎች አርሞ ትምህርት ቤቱም ሆነ ቤተክርስቲያኑ ወደ አንዱ አገር ማጠፍ አይችልም: በጠቅላላው ኮሚሽኑ ከላይ የተጠቀሱ ሁኔታዎችንም ሆነ ተመሳሳይ ጉራማይሌ ሁኔታዎችን ለማስተካከል አይፈቀድለትም: በዚህም ተጐጂ የሚሆኑት የድምበር መስመሩ በሚያርፍበት አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ ያለው አማራጭ ሁለቱ ወገኖች ተስማምተው እርምት ማድረግ ብቻ ነው:: እርምት ለማድረግ ስምምነት ሳይደርሱ ውሳኔው እንደወረደ ሥራ ላይ ማዋል ሊኖር ነው በኢትዮጵያና በኤርትራ ባለሥልጣናት መሃከል ባለው ግትርነት ጥላቻ ምክንያት እንዲህ ዓይነቱ መግባበት ደርሰው እርምት ለማድረግ ይስማማሉ ብሎ መጠበቅ አዳጋች ነው::

በኤርትራና በኢትዮጵያ ድምበር ኮሚሽን ውስጥ ይሠራ የነበር በኂላም ወደ ናይጂሪያ ካሜሩን የድምበር ኮሚሽን ተዛውሮ የዚህ ጸሐፊ የሥራ ባልደረባ አሜሪካዊ የሁለቱን አገራት



ባለሥልጣናት ሲገልጽአቸው "እንደ ሚስማር የጠጠሩ" (tough as nail) ናቸው ብሎአል:: ከሁለቱም መግባበት መጠበቅ ስህተት መሆኑን ገልጾአል::

የኢትዮጵያ ተወካዮች ወደ ፊት እንደምናየው ዋና ዋና የአገሪቱ ጥቅሞችን አስረክበው በጭፍጫፊ ላይ ግትር መሆን ጠቃሚነቱ እምን ላይ መሆኑ እነርሱ ብቻ ናቸው የሚያውቁት::

## 5.7. የውሉ አፈፃፃምና የኢትዮጵያ የተዛባው አካሄድ

•በናይጀርያና በካሜሩን መሃከል የድምበር ችግር ተፈጥሮ ጉዳያቸው ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወስደው ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሲሰጥ የድምበሩ መስመር አንዱን ከተማ ለሁለት ሲከፍል ከዚህያም አልፎ አንድን ቤት ግማሹን በናይጀርያ በኩል ሲያስቀመጠው ሌላው ግማሽ በካሜሩን በኩል ሲሆን ሁለቱ ወገኖች ተስማምተው መስመሩን አስተካክለው ቤቱና የከተማው ክፍል ወደ ካሜሩን እንዲታጠፉ ሆነ:: የካሜሩንና የናይጀርያ የወሰን ድርድር መግባባት የነበረበትና በሰለጠነ መንገድ የተስተናገደ ስለነበረ ከነዚህም የከፉ ውስብስብ ችግሮችን ወደ ፊት እንደምናየው በመግባባት ፈትዋትል[124]:

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የነበረው ጦርነት እንደተጠናቀቀ በየትኛው አገር ጠያቂነት እንደሆነ አይታወቅም ለግልግል ደኅንነት ወደ አልጀርስ ማቅናታቸው ከዚህ በፊት ተገልጾአል:: የሌሎች በጦርነት ውስጥ የነበሩት አገሮች ተሞክሮ እንደታየው ከሆነ በአንድ ጦርነት አሸናፊ የሆነ አገር የጠላትን ግዛት ይዞ እንደሆነ በዚያው በያዘው ቦታ እረግቶ ተሸናፊው ተኩስ አቁም ስምኖ ለግልግል አስቀድሞ ጎያቂ ያቀርባል:: ግልግሉ ተጠናቅቆ ስምምነት እስኪደርሱ ድረስ አሸናፊው የያዘው መሬት ለወደታደራዊ እንቅስቃሴ ጠቃሚነት ያለው ገገር መሬት ከሆነ

[124] Case Concerning the Land and Maritime Boundary between Cameroon and Nigeria (Cameroon V. Nigeria and Equatorial Guinea Intervening) 10 October 2000 Judgment

ወይንም ለወደፊቱ ጠላት ጥቃት ሊሰነዝርበት አመቺ የሆነ ቦታ ከሆነ ጠላቱ በድጋሚ እንደማይወረው ዋስትና ሲሰጠውና ሌሎች ሌሎች ግዴታዎችም ውስጥ ካስገባው በኋላ የያዘውን የሰው መሬት ለቅቆ ይወጣል።

ለምሳሌ እስራኤል እ.አ.አ በ1967 ዓ.ም በአረቦች ከተወረረች በኋላ በጦርነቱ አሸንፋ ከያዘቻቸው የአረብ ግዛቶች አንዱ ኢየሩሳሌም አናት ላይ ያለው የሶርያ ግዛት ጐላን ሃይትስ ነው። ጐላን ኃይትስ ላይ ሆኖ በቀጥታ ኢየሩሳሌምን መቆጣጠር ስለሚያስችል ሶርያ ለእሥራኤል እውቅና እስከትሰጥ ድረስ እስራኤል ጐላን ሃይትስን አለቅም ብላ እነሆ ለአርባ አራት ዓመታት ይዛባት ትገኛለች። ዓለም አቀፍ ሕብረተ ሰብም ሆነ የተባበሩት መንግሥታት ጐላን ሃይትስን ከእሥራኤል ለማስለቀቅ የወሰደው ምንም እርመጃ የለም። በተመሳሳይ መልኩ ኢትዮጵያም ለደህንነትዋ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን አሳብ ወደ ኢትዮጵያ እስኪታጠፍ ወይንም ከኤርትራ ጋር አሰብን አስመልክቶ ሌላ ስምምነት እስኪደረግ ድረስ ከያዘቻቸው የኤርትራ ግዛት አልወጣም ብትል ድሮውንም ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራት በደገፈው ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ወቀሳ አይደርስበትም ነበር። ስለዚህ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማጠፍ ከሚያስችሉ ብዙ ዕድሎች አንዱ ይኸው ሲሆን በዚህና በተመሳሰይ ወደፊት በሚጠቀሱ እድሎች ኢትዮጵያ ሳትጠቀምባቸው አልፏአል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል በተደረገው ጦርነት ኢትዮጵያ እንደ አሸናፊነትዋ ከአሸናፊነት የሚመነጩ መብቶች አልተጠቀመችባቸውም። ይልቁንም በሕገወጥ አልጀርስ ስምምነት ምክንያት ለጉዳት ተዳረገች።



## ምዕራፍ 6

## 6. በአልጀርስ ስምምነት መሠረት የተቋቋመው የድምበር ኮሚሽን አመሠራረትና ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ሲገመገም

በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል የነበረው ቁጥራቸው እስከ ዛሬም በሁለቱም ባላጋራዎች ያልተገለፀ በጣም ብዙ ኢትጵያውያንና ኤርትራውያን ወንድማማቾችና እህትማማቾች የተላለቁበት ጦርነት፤ ብዙ ዋጋ ብትከፍልም በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተደምድሞ የሁለቱም አገሮች መሪዎች በወቅቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀ መንበር በነበሩት በአልጀሪያው ፕሬዝደንት በአብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ አደራዳሪነት ሰላም ለማውረድ፤የድምበር ስምምነት ለመፈራረምና ለመካሰል ወደ አልጀሪያ ዋና ከተማ አልጀርስ አቀኑ።

ድርድሩ በአጭር ቀናት ውስጥ ተጠናቅቆ በተኩስ አቁም ስምምነት፤ የድምበር ኮሚሽንና የካሣ ኮሚሽኑ በሚያቋቁመው ሰነድ ላይ የሁለቱም አገሮች መሪዎች አቶ መለስ ዜናዊና አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ፈርመው ጥላቻና ቂም በሚያንፀባርቅ መልክ ተጨባብጠው በሌላ ወቅት እንደተለመደው ሳይተቃቀፉና አንዲት ቃል ሳይለዋወጡ ተለያዩ።

በሁለቱ ወንድማማች "የሐበሻ" መሪዎች (አቶ ኢሣያስ ቢክዱም) አንድ የአረብ አገር መሪ መሃል ገብቶ ሲያጨባብጣቸው ማየት ሕሊናን የሚሰብር ትዕይንት ነበር። እ.አ.አ. በዲሴምበር 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሁለቱ መሪዎች ድንበር ማካለሉ በቅኝ ግዛት ውሎችና በሌሎች ሕጐች መሠረት እንዲሆን ተስማምተው ሲጨባበጡ የተላለፈው መልእክት የኢትዮጵያ የባህር በር ተዘጋ፤ "ቡቃ ተዘጋ" የሚል ለኢትዮጵያውያን አስደንጋጭ መልዕክት ነበር።

የአልጀርስ ስምምነትና ውሰኔ ከውጫሌው ውል ባልተናነሰ ምናልባትም በከፋ መልኩ በአገር ላይ ጉዳት ያደረሰ ውል ስለሆነ ከድርድሩ ቀጠና (Venue) አመራረጥ ጀምሮ የሊቀ መንበሩ አሰያየም፣ለድርድሩ መሠረት የሆኑ ሕጎችንና የዳኞቹ አመራረጥና ገለልተኛነት የድርድሩ አካሄድ መመርመር ያስፈልጋል።

እነዚህን የ1900ዓ.ም፣ 1902ዓ.ም እና የ1908ዓ.ም ስምምነቶችን በሥራ ላይ ለማዋል በአልጀርስ የተፈረመው ስምምነት በኢትዮጵያ ላይ ዘላቂ ጉዳት የሚያስከትል የኢትዮጵያን የባህር በር የሚዘጋና አሰብን ለኤርትራ የሰጠ ስምምነት ሲሆን፤ ይህ የአልጀርስ ስምምነት አጼ ምኒልክ እንደፈረሙአቸው "ውሎች" በኢትዮጵያ ላይ በግድ የተጫነ ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግስት ሕወሓት/ኢሕአዴግ ፈቅዶ (ምናልባትም ለምኖ) ዳኛ መርጦ፤ ሥልጣናቸውና የሚዳኙበት ሕግ ወስኖ የገባበት ስምምነት ነው።

የዚህም ውል ዋናው ዓላማ የኢትዮጵያና የኤርትራ የጋራ ድምበር የሚያካልል አምስት ዳኞች የያዘ ኮሚሽን አቋቁሞ ኮሚሽኑ የተባበሩት መንግሥታት፤ የአውሮፖ ኅብረት፤ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅትና የአሜሪካ ተወካዮች በአስፈጻሚነት በተገኙበት የተቋረጠ ይግባኝ የሌለበት ውሳኔ መስጠትና ድምበር ማካለል ነበር።

## 6.1. የየአገራቱ ተወካዮች ማንነት

በኮሚሽኑ ፊት የኢትዮጵያን ቡደን የመሩ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ክብረ ወሰን የያዙት በጊዜው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት የሕወሓት መሥራች አባል አቶ ሥዩም መስፍን ሲሆኑ በተባባሪነት ደግሞ የህግ ባለሙያ የሆኑት አምባሳደር ፍሰሐ ይመር ተመድበው ነበር። እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አባል የሆኑ አንድ የሕግ ባለሙያ የመንግሥት ባለስልጣን በቡድኑ ተጨምረው፣ ሌሎች አስራ አንድ የውጭ አገር ዜጎችን ጨምሮ በጠቅላላው ኢትዮጵያ አስራ አራት አባላትን በማያካትት ቡድን ተወክላ ነበር። ወሳኝ በሆነው በሕግ አማካሪነትና በጥብቅናው ዘርፍ ማንም ኢትዮጵያዊ አለመመደቡ ሊሠመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ናቸው ክርክሩን አዘጋጅተው በድምበር ኮሚሽኑ ፊት ቀርበው



የሚሟገቱት ። ሌሎቹ የቡድኑ አባላት አማካሪዎች ናቸው ማለት ይቻላል። የአንድ ኢትዮጵያዊ እንኳን በቡድኑ መካተት ወደ ፊት እንደሚታየው ግልጽ የሆኑ የኤርትራና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ የተሠሩ ስህተቶችን ማረም ያስችል ነበር።

የኤርትራው ቡድን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሊ ሰይድ አብደላ ሲመራ ተባባሪአቸው ደግሞ ፕሮፌሰር ሊያ ብሪልሜየር ( Lea Brilmayer) ነበሩ። የኤርትራ ቡድን በውስጡ ሦስት የመንግስት ባለስልጣናትና አንድ የኤርትራ ዩኒቬርሲቲ ፕሮፌሰር ያቀፈ ሲሆን፤ እንዲሁም አስር የውጭ ዜጎች አካትቶ በጠቅላላው ኤርትራ በአሥራ አራት ሰዎች ስትወከል በሕግ አማካሪነትና በጥብቅናው ዘርፍ ከውጭ አገር ዜጎች በተጨማሪ የአሥመራ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰር የማነ ምሾጊና ተመድበው ነበር[125]።

ሁለቱ ቡድኖች ሲነፃፀሩ ኢትዮጵያ በኮሚሽኑ ውስጥ አስራ አራት ሰዎች ስታሠማራ ኤርትራም እንደዚሁ አስራ አራት ሰዎችን መድባ ነበር። በኢትዮጵያ በኩል ሁሉም የመንግሥትን አቋም የሚያቀነቅኑ ግለሰቦች ሲሆኑ የአልጀርስን ስምምነት የተቀበሉና የኢትዮጵያ የባህር በር እንዲዘጋ የተስማሙ ነበሩ ማለት ይቻላል። የኢትዮጵያን የባህር በር መዘጋት የሚቃወሙ ቢሆኑ ኖሮ ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የጫነቻቸው የኢትዮጵያ የባህር በር በእርግጠኝነት የሚዘጉና የፈረሱ የቅኝ ግዛት ውሎችን ተቀብለው ኢትዮጵያን ወክለው በድርድሩ ባልተገኙም ነበር።

ሁለቱ ቡድኖች የሚለያቸው ነገር ቢኖር የኤርትራ ዜጎች በኮሚሽኑ ውስጥ የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ ሲሆን የኢትዮጵያውያን ተሳትፎ አነስተኛ ነበር ማለት ይቻላል። ከላይ እንደተጠቀሰው ኤርትራ ከውጭ አገር ዜጎች ሌላ በሕግ

125 Eritrea-Ethiopia Boundary Commission Decision Regarding Delimitation of the Border between the State of Eritrea and the Federal Democratic Republic of Ethiopia, The Hague 13th day of April 2002 (unpublished)

አማካሪነትና በጥብቅናው ዘርፍ አንድ ኤርትራዊ ስትመድብ በዚህ እጅግ ወሳኝ በሆነ ዘርፍ ማንም ኢትዮጵያዊ ካለመመደቡም ሌላ ኢትዮጵያን የወከሉ የውጭ አገር ዜጎች አንዳቸውም በኢትዮጵያ ጥናት ማለት በሕግ፣በኢትዮጵያ ታሪክና ባሕል እውቀት የተካኑ ነበሩ ለማለት የሚያስደፍሩ አልነበሩም። ይህም ስለኢትዮጵያ የዕውቀት ማነስ በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ እንዴት እንደተንፀባረቀ ወደፊት እናየዋለን። በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም ዙሪያ በህግ ፣በታሪክና በሥነ መንግሥት እውቀታቸውና በሥራ ተሞክሮአቸው የታወቁ በትላልቅ ዩኒቨርስቲዎችና ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት የላቀ ሚና የሚጫወቱ ሌላው ዓለም ግልጋሎታቸውን የሚፈልገው ኢትዮጵያውያን በዚህ ትልቅ አገራዊ ጉዳይ እርዳታቸውን እንዲለግሱና ብሔራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለምን እንዳልተጠየቁ ኢሕአደግ ብቻ ነው የሚያውቀው። እነዚህ ኢትዮጵያውያን እነደ ፈረንጆቹ ዘጠኝ ሚልዮን ዶላር ወጪ ሳያስወጡ አገራቸውን በዚህ ጉዳይ በነፃ ለማገልገል ፈቃደኛ ይሆኑ እንደነበረ መጠራጠር አይቻልም።

## 6.2. የድርድሩ የጊዜ ሰሌዳ

ሁለቱም አገራት ስምምነቱ በተፈረመ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ዳኞች መርጠው ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ማሳወቅ እንደሚጠበቅባቸው ውሉ ይደነግጋል ። ከዚያም በኋላ በሰላሳ ቀናት ውስጥ የኮሚሽኑ ሊቀ መንበር መመረጥ ሲኖርበት በተከታዩ አርባ አምስት ቀናት ውስጥ ደግሞ እያንዳንዱ አገር አለኝ የሚለውን መብትና ማስረጃዎቹን አሰባስቦ በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ፀሐፊ ያቀርባል።

ኮሚሽኑ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ተሰብስቦ ሥራውን እንዲጀምርና ውሳኔው በስድስት ወራት ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበት በስምምነቱ ተደንግጎአል[126]። ይህ ወሳኝና የኢትዮጵያን

[126] Eritrea-Ethiopia Border Commission Decision, Ibid



የባሕር በር የሚዘጋና የኤርትራ ዳር ድንበርን የሚያረጋግጥ ውሳኔ በተፈረመ ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ስምምነት ላይ ተደረሰ።

ኮሚሽኑም ይህንን የጊዜ ሰሌዳ ጠብቆና አክብሮ ውሳኔውን ሰጠ። ከመጀመሪያውኑ ኢትዮጵያ ጦርነቱን ባሸነፈች ማግስት ኢሕአዴግ ለድርድር ተጣድፎ አልጀርስ የሄደበት ምክንያት ግልጽ እንዳልነበረ ሁሉ አሁንም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚነካ ብብዙ አንፃሩ የወደፊት የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ የሚወስንና የኢትዮጵያን የባህር በር የሚዘጋ እጅግ በጣም ትልቅ አገራዊ ጉዳይ በአምስት ግለሰቦች በሆይ ሆይታ ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ የኢሕአዴግ መሪዎች እንዴት ሊስማሙ እንደቻሉ ግር ይላል።

ጦርነቱ ተደምድሞ የህይወት መጥፋትና የንብረት መውደም ከቆመ በኋላ ለድርድር መጣደፍ ለምን እንዳስፈለገ ግልፅ አይደለም። ሆኖም ለዚህ ሁሉ ጥድፊያ በጊዜው ኢሕአዲግ የሰጠው ሊታመን የሚያዳግት ምክንያት የጦርነቱና የድምበር ውዝግቡን ዘግተን ፊታችንን ወደ ልማቱ ማዞር እንፈልጋለን የሚል ነበር።

የድንበሩን ጉዳይ የሚከታተሉ ዳጎስ ያለ ገንዘብ የሚከፈላቸው ጥቂት የውጭ አገር ዜጎችና ጥቂት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረቦች በኮሚሽኑ ሥራ መጠመድ የልማቱን እንቅስቃሴ በምን መልኩ ሊያደናቅፍ እንደሚችል ግልጽ አይደለም።

መንግሥት ጊዜ ወስዶ ሕዝብ እንዲወያይበት ዕድል ሰጥቶ በዓለም አቀፍ ሕግና በወሰን አካለል ተሞክሮ ያላቸው ኢትዮጵያውያንን አማክሮ ቢሆን ኖሮ ምናልባትም የኢትዮጵያን የባህር በር የሚዘጋ አሳዛኝ ስምምነት ተፈራርሞ ኮሚሽኑ የሰጠውን አሳፋሪ ውሳኔ በኢትዮጵያ ላይ ባልተጫነም ነበር። ባድመንና ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶችን ኮሚሽኑ ለኤርትራ ሲፈርድ ኢሕአዴግ "ሱሪ ባንገት" ሆኖበት የውጭ ጉዳይ ሚኒስተሩ በጠራራ ፀሐይ ባድመ ለኢትዮጵያ ተፈርዶላታል ሲሉ ሕዝቡን አሳሳቱ።

በሌሎች አገራት የተከሰቱ የመሬት ይገባኛል ጥያቄዎችና የድምበር ውዝግቦች እልባት ለማግኘት ከአምስትና ስድስት እንዳንዴም ስምንት ዓመታት እንደሚፈጁ በተደጋጋሚ ታይቷል።

በካሜሩንና በናይጄርያ መሃከል የነበረው ይህ ጸሐፊ በህግ አማካሪነት የተሳተፈበት የመሬት ይገባኛል ጥያቄ የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመስጠት ስምንት ዓመታት ሲፈጅ፤ ውሳኔ ከሰጠም በኋላ የተባበሩት መንግስታት፣ የካሜሩንና የናይጄርያ ወኪሎችን ያቀፈ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ኮሚቴው ሕዝቡን አወያይቶ ወሰን ለማካለል ሌላ ሦስት ዓመት አስፈልጉታል።

በጠቅላላው በናይጄርያና በካሜሩን መሃከል የነበረውን የመሬት ይገባኛል ጥያቄ ለመዝጋት ከአሥር ዓመታት በላይ ፈጅቶአል። እንዲሁም በቻድና በሊቢያ መሃከል የነበረውን የወሰን ውዝግብ እልባት ለመስጠት ከሦስት ዓመታት በላይ ወስዶአል።

የባህር በርን የሚዘጋ፣ ባድመን፣ኢሮብን፤ጸረናና ከፊል አፋርን ሌሎችም የኢትዮጵያ ግዛቶችን ለኤርትራ አሳልፎ የሚሰጥ ውዝግብ በሁለት መቶ ሳማንያ አምስት ቀናት ውስጥ ሲጠናቀቅ በእንፃሩ በበግ ሽያጭ የተነሳ የፍርድ ቤት ክርክር እንኳን መጌቶቱ የማይደገፍም ቢሆን ከአስራ ሁለት ወራት በላይ እንደሚወስድ ይታወቃል።

## 6.3. የድርድሩ ቀጣናና የአደራዳሪው ማንነት

ኢትዮጵያና ኤርትራ ተደራድረው ስምምነቱን የፈረሙት በአልጄርያ ዋና ከተማ በአልጄርስ መሆኑ ይታወሳል። አልጄርያ የአረብ አገርና የዓረብ ሊግ አባል ስትሆን በኤርትራ የመገንጠል ጥያቄ ገና ከጥንስሱ እስከ ድምዳሜው ድረስ ለሻቢያና ለጀብሃ የማቴርያልና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ትሰጥ እንደነበረች ለኢሕአዴግ የተሰወረ አልነበረም። ከዚህ በረከትም ሕወሓትም ሳይቋደስ እንደልቀረ በእርግጠኝነት መናገር ይችላል።



በዚሁ ድርድር ዋናው አጋፋሪ የነበሩት ሚስተር አብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ የወቅቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር አገራቸውን ለረጅም ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነትና በፕሬዝደንትነት አገልግለዋል። አልጄርያ ከሻቢያና ከጀብሃ ጋር ለነበራት ግንኙነት ፖሊሲ ቀራጺና (አርኪቴክት) ለኤርትራ መገንጠል ሌት ተቀን የሠሩ ሰው ናቸው።

እኚህ ሰውዬ የአልጄርያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የአፍሪካ አንድት ድርጅት ዋና ቢሮ ከአዲስ አበባ እንዲነሳ ሲጥሩ የነበሩ ሲሆን በዚህ ጉዳይ በጊዜው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከነበሩት ከክቡር ከተማ ይፍሩ ጋር አንድ ስብሰባ ውስጥ የኃይል ቃል ተለዋውጠው እንደነበር በስብሰባው ተገኝተው የነበሩ አንድ የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ ለዚሁ ፀሐፊ ገልጸውለታል። ስለሆነም ድርድሩ የተካሄደው በገለልተኛ አገር ሳይሆን ከኢትዮጵያ ጋር በጠላትነት የተሠለፈ አገር ውስጥ ነው። እንዲሁም አደራዳሪው ታማኝና ገለልተኛ ሳይሆኑ እንዲያውም ኢትዮጵያ እንድትፈርስ ይፈልጉ ከነበሩት አረባዊ ባለስልጣናት አንዱ ነበሩ ማለት ነው።

ኢትዮጵያና ኤርትራ ሁለቱም የጥቁር ሕዝብ አገሮችና የጥቁር አፍሪካ አካል መሆናቸው እየታወቀ በአደራዳሪነት ከፍተኛ ተሞክሮ ያላቸው አፍሪካውያን እያሉ ለድርድር ለምን አረብ አልጀርያዊ ተመረጠ? የአረብ መሪዎች በኢትዮጵያ ላይ ያላቸው አስተያየት እየታወቀ አብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ ገለልተኛና ታማኝ አደራዳሪ ሊሆኑ እንደማይችሉ ለምን ተዘነጋ?

ምናልባትም አብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ ለድርድሩ ሊቀ መንበርነት የተመረጡት በጊዜው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀ መንበር ስለነበሩ ነው የሚል መልስ ይሰጥ ይሆናል። ሆኖም ድርድሩም ሆነ ስምምነቱ የግድ አልጄርያ ውስጥ፤ አደራዳሪውም የግድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀ መንበር መሆን ነበረባቸው የሚል ህግ የለም። ብዙ የአፍሪካ አገራት በመሃከላቸው የሚነሱ ውዝግቦች ከአፍሪካ አንድነት ውጭ ተደራድረው ወይንም ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቀርበው ውዝግቦቻቸውን የቋጩባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው። ምናልባትም ድረድሩ አልጀርስ ከተማ ውስጥ

በመሆኑ አደራዳሪውም አረባዊ ፕሬዝደንት መሆናቸው በስምምነቱ ውጤት ላይ ተጨባጭ አሉታዊ ውጤት ይኑረው አይኑረው በውል ማረጋገጥ አይቻል ይሆናል። ሆኖም ግን ጥርጣሬው ተገቢ ከመሆኑም በላይ እጅግ ቢያንስ ስምምነቱን ገና ከመነሻው የጥርጣሬ ድባብ የለበሰ፤ለኤርትራ የሚያደላ የሚመስል፤ ተአማኒነቱ የሳሳ አድርጉታል።

## 6.4. የድንበር ኮሚሽኑ ዳኞች ማንነት

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የነበረውን የድንበር ውዝግብ መርምረው ፤ የቅኝ ግዛት ውሎችን ቃኝተው አግባብነት ያላቸው የዓለም አቀፍ ሕጎችንና የአፍሪቃ አንድነት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔን ዋቢ በማድረግ ይግባኝ ሊባልበት የማይቻል ውሳኔ እንዲሰጡ ኤርትራና ኢትዮጵያ ሁለት ሁለት ዳኞች መድበው እነዚህ አራት ዳኞች ሊቀ መንበር እንዲመርጡ ስምምነት ላይ መደረሱ ከለይ ተገልጸአል።

ባለጉዳዩቹ ለዳኞቹ የሰጡአቸው መመሪያዎች በስምምነቱ በአንቀጽ 4 የተቀመጡ ሲሆን፤ እነዚህም ኢትዮጵያ ከጣልያን ጋር የተፈራመቻቸው የ1900 ዓ.ም፤የ1902 ዓ.ም እና የ1908ዓ.ም "ውሎች" አግባብነት ያላቸው የዓለም አቀፍ ሕጐች እንዲሁም በካይሮ በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት በ1964 ዓ.ም የመሪዎች ጉባኤ በቁጥር AHG (Res16(1) የአፍሪካ አገራት ነፃ በወጡበት ወቅት የነበራቸው ድንበር መከበር አለበት የሚለውን መርህ ተከብሮ ወሰኑ እንዲካለል ተስማሙ። ዳኞቹ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ሰብአዊ ርህራሄ፣ ፍትሐዊ አስተያየት አመክንዮ (ex acqua et bono) የመሳሰሉት ከግንዛቤ እንዳያስገቡ መመሪያው አገደ[127]። በዚህም መሠረት ወሰኖቹን ለማካለል ሊረዱ ይችሉ የነበሩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፤ ዓለም አቀፍ ልምዶች፤ የሰለጠኑ አገራት የተቀበሉአቸው የሕግ መርሆች፣ የህግ ጠበብት የደረሱአቸው ጽሁፎችና የተለያዩ የፍርድ ውሳኔዎች መጥቀስ አይቻልም ማለት ነው።

[127] Eritrea-Ethiopia Border Commission Decision, ibid.



ይህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የካይሮው የመሪዎች ጠቅላላ ጉባዔ የ1964 ዓ.ም ውሳኔ አግባብነት ያለው ከቅኝ ግዛት ነፃ ለሚወጡት አገራት ሲሆን የኤርትራና የኢትዮጵያ ግንኙነት የቅኝ ገዢነትና ተገዢነት ስላልነበር ይህ መርህ ለኮሚሽኑ ውሳኔ በሌላ ቦታ እንደተብራራው ግብአት ሊሆን አይችልም ነበር።

ከአራቱ ዳኞች ኤርትራ ሚስተር ጃን ፓልሰን (Mr Jan Paulson) እና ዳኛ ስቴፈን ሽዌብል (Judge Stephen Schwebel ) ስትመርጥ ኢትዮጵያ ደግሞ ልዑል ቦላ አዴሱምቦ አጂቦላ (H.E Prince Bola Adesumbo Ajibola) እና ሰር አርተር ዋትሰን (Sir Arthur Watts) መደበች። ጥቂት ቆይቶ ኢትዮጵያ ባልታወቀ ምክንያት የሚስተር ጃን ፓልሰን የኮሚሽኑ አባልነት ስለተቃወመች ሰውየው ከኮሚሽኑ አባልነት እራሳቸውን አገለሉ።[128]። የኮሚሽኑ ዳኞች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።*

1. ፕሮፌሰር ኤሊሁ ሉተርፓክት -ፕሬዚዳንት

   Pro. ElihuLauterpacht President

2. ልዑል ቦላ አዴሱምቦ አጂቦላ

   Prince Bola Adesumbo Ajibola

3. ፕሮፌሰር ማይክል ራይስማን
   Prof.Michael Reisman.
4. ሰር አርተር ዋትስ
   Sir Arthur Watts.
5. ዳኛ ስቴፈን ሽዌብል
   Judge Stephen Schwebel

[128] Ibid

* የዳኞቹ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፤ ቀደም ሲል በኃላፊነት የተመደቡባቸው ሥራዎች ከኢንተርኔት አይቶ ከሙሉቱ ቡድን የትኛው እንደሚሻል መገመት ይቻላል።

ኮሚሽኑ የዳኝነት ሥርዓቱ አጠቃላይ ወጪዎች የዳኞቹ ክፍያንም ጨምሮ የሁለቱ አገራት መንግስታት እንደሚሸፍኑ ሲደነግግ ኮሚሽኑ ከተባበሩት መንግስታት የገንዘብ እርዳታ ከተለገሰው እንዲቀበል በስምምነቱ ተፈቅዶለታል። የተባበሩት መንግስታት የካርታ ክፍል ኃላፊ (U.N.Cartographer) የኮሚሽኑ ፀሃፊ ሆነው እንዲያገለግሉ ሲመደቡ የቋሚ ግልግል ፍርድ ቤት (Permanent Court of Arbitration) ዋና ጸሃፊ ደግሞ በሬጂስትራርነት እንዲያገለግሉ ተመርጠው ኮሚሽኑ ሥራውን ወዲያውኑ ጀመረ።

አንዳንድ ኢትዮጵያውያን በኮሚሽኑ ገለልተኛነትና አወቃቀር ቅሬታቸውን አሰምተዋል። ፕሮፌሰር ተኮላ ወርቅ ሐጎስ የኮሚሽኑን አወቃቀር ሲነቅፉ "የኮሚሽኑ አባላት ቀራ ጠበቆች ሲሆኑ እንደማንኛውም ጠበቃ ገንዘብ የሚከፈላቸው ጉዳዩ እምብዛም የሚያሳስባቸው አይደሉም"[129]ይላሉ። ፕሮፌሰር ተኮላ በመቀጠል ሰብሳቢው ዳኛ ፕሮፌሰር ሎተርፓክት ገለልተኛነታቸውና የግል ታማኝነታቸው አጠራጣሪ ስለሆነ ከኮሚሽኑ አባልነትና ሰብሳቢነት መነሳት እንዳለባቸው በጊዜው አሳስበው ነበር። እንዲሁም ኢትዮጵያና ኤርትራ ያዋቀሩት ኮሚሽን በቋሚ የግልግል ፍርድ ቤት (Permanent Court of Arbitration) ስር ሆኖ የሚሠራ ሲሆን ይህ ፍርድ ቤት የተቋቋመበት ኮንቬንሽን ኤርትራ እ.ኤ.አ. በ1997ዓ.ም ተቀብላው ስትፈርም ኢትዮጵያ ስላልፈረመች ዳኞቹ ለኤርትራ ያደላሉ በማለት ፕሮፌሰር ተኮላ ስጋታቸውን ገልጸው ነበር[130]።

## 6.5. ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወይስ የግልግል መድረክ

አብዛኛዎች አገራት ከጎረቤቶቻቸው ጋር የድንበር ውዝግብ በሚፈጠርበት ጊዜ ጉዳያቸው የተባበሩት መንግሥታት ዋነኛ

[129] Tecola W. Hagos, Professor "Aklilu Habtewold: In the Footsteps of a great International Law Jurist, Disqualification of Lauterpacht, 30 Oct. 2003

[130] Ibid



የፍትሕ አካል ቋሚ ቢሮው ሄግ ወደ ሆነው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) ወስደው ተከራክረው ዳኝነት ያገኛሉ። ጉዳዩን የሚያዩ 15 ዳኞች በችሎት ተሰይመው ሲሆን እያንዳንዱ ዳኛ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔና በጸጥታው ምክር ቤት የተሾመ ነው። በተጨማሪም የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ደንብ አንቀጽ 31 ፓራግራፍ 2 እና 3 በሚደነግገው መሠረት በችሎቱ ላይ እያንዳንዱ አገር ከዜጎቹ አንዳንድ ተወካይ ጊዜያዊ ዳኛ (Judge ad hoc) የሚሰይም ሲሆን ይህ ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር እኩል ሥልጣን ያለው ነው[131]። የዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመድረስ የጊዜ ገደብ ሳያስቀምጥ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ጊዜ ወስዶ ውሳኔ ይሰጣል።

ዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ለዳኝነቱ መሠረት የሚያደርጋቸው ብዙ ሕግጋት አሉ። እነዚህም፤ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሃገራቱ መሃከል የተደረጉ ውሎች ካሉ፣ ዓለም አቀፍ ልምዶች፣ የሰለጠነው የዓለም ሕዝብ የተቀበላቸው የህግ መርሆዎች፣ ቀደም ሲል የተሰጡ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች፣ የሕግ ልሂቃን የደረስዋቸው ጽሁፎች፣ ሲሆኑ በተጨማሪም ባለጉዳዩቹ ከተስማሙ- ፍትሕና ርትዕ፣ ሰብአዊ እርህራሄ (ex acquo et bono) ለዳኞቹ ውሳኔ ግብዐት ሊሆኑ ይችላሉ። የእነዚህ ለውሳኔ መሠረት የሚሆኑ የተለያዩ ሕጎች ዳኞች ፍትሕ ላይ እንዲደርሱ ይረዱአቸዋል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የአልጀርሱ ስምምነት ግን በዋነኛነት ለውሳኔው ግብአት ያደረገው የቅኝ ግዛት ውሎች ሲሆኑ በእነዚህ በኢትዮጵያ ላይ በግድ በተጫኑ ውሎች መሠረት ኢትዮጵያ ፍትሕ አግኝታለች ማለት አይቻልም። ለዚህም ነው ውሳኔው ፍጹም ኢፍትሐዊ በመሆኑና ባድመንና ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች አሳልፎ ለኤርትራ የሚሰጥ ስለሆነ ኢሕአዴግም ይህ ሁኔታ ለሥልጣኑ አደገኛነቱ ስለተረዳ በመርህ ደረጃ ተቀብዬዋለሁ ቢልም ውሳኔውን ሲተገብረውና ከኤርትራ ጋር ምስሶ ወይንም ችካል ለመትከል ፈቃደኛ አልሆነም። ውሳኔውን በመርህ ደርጃ ተቀብዬአለሁ ማለት ደግሞ ትርጉም የሌለው አባባል ነው።

[131] International Court of Justice, Article 31, para. 2 and 3.

የኢትዮጵያና የኤርትራ የወሰን ውዝግብ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቢቀርብ ኖሮ ኢጣልያና ኢትዮጵያ የተፈራረሙአቸው ውሎች ፍርድ ቤቱ ውድቅ እንደሆኑ ተረድቶ ሌሎች ከላይ የተጠቀሱትን ሕግጋት ተጠቅሞ ለኢትዮጵያ የቆመ ተከራካሪ ኖሮ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል ቢጠይቅ ኖር ውሳኔው የኢትዮጵያን የባህር በር ላይዘጋ ይችል ነበር። ይልቁንም ፍርድ ቤቱ ፍትሐዊና ሰብአዊ አስተያየትና አመክንዮን ከግምት በስሚያስገባ 90 ሚልዮን ሕዝብ ቀደም ሲል በታሪክ፣ አሁንም ለአርባ ዓመት መግቢያ መውጫ የነበረውን አሰብን ኮሚሽኑ ለኤርትራ ሰጥቶ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ትሁን ብሎ መፍረድ እጅግ አስቸጋሪ ይሆንበት ነበር።

## 6.6. የክርክር ፍሬ ነገሮች

የሁለቱ አገራት ጠበቆችና ዳኞች መደበኛ ችሎት ባልሆነ ስብሰባ የክርክሩ አካሄድ እንዴት መሆን እንዳለበት ከተስማሙ በኋላ እ.አ.አ ከዲሴምበር 10 እስከ 21, 2001 ዓ.ም. የፍርድ ቤት መቀመጫ በሆነው "በሰላም ቤተመንግሥት" (Peace Palace) በሄግ የመጀመርያ የቃል ክርክር ከኢትዮጰያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ስዩም መስፍንና ከኤርትራው አቻቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሚስተር አሊ ሳይድ አብደላ ከተደመጠ በኋላ በጠበቆቻቸው መሃከል የቃል ክርክር ተደረገ። በመከተልም ኤርትራ ባቀረበችው አቤቱታ (Memorial) በአያያዘችው ማስረጃ መሠረት ያመለከተችው ድንበር ይፅደቅልኝ የሚል ሲሆን የኢትዮጵያ ተወካዮች በተደጋጋሚ የ1900፣ 1902፣ 1908 ዓ.ም. ውሎች የሚጠቅሱአቸውን ወሰኖች እንዲፀድቁላቸው ጠየቁ።

የኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ የኢትዮጵያ ተወካዮች አንዳቸውም አንድም ጊዜ ትንፍሽ አላሉም። በኢትዮጵያ ተመርጠው የኮሚሽኑ አባል የነበሩት በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት አገራቸውን የወከሉና እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት በሶማሌያንና በናይጀርያ በጋራ ኮሚሽን የአገራቸውን ቡድን የመሩ ልዑል ቦላ አጂ ቦላ በጣም የሚቀልዱ ሰው ሲሆኑ ከዚህ ጸሐፊ በተገናኙ ቁጥር "አሰብን፣ እሰጥሃለሁ" እያሉ ይቀልዱበት ነበር።



ፀሐፊውም የኢትዮጵያን መጻኢ እድል የሚወስን ከባድ ጉዳይ እንደሆነ ልዑሉን ከማስገንዘብ አልቦዘነም።

ኮሚሽኑ በመግቢያ ምዕራፍ ውስጥ የድንበር ውዝግቡን መሠረትና ታሪካዊ አመጣጡ በሚተነትንበት ጊዜ አንዳንድ ስህተቶችን አስፍሮአል። ስለኤርትራ ታሪክ በሚያትትበት ጊዜ አብዛኛው ኤርትራ እ.አ.አ ከ1880 ዓ.ም. በፊት የአቶማንና የግብጽ ይዞታ እንደነበረች ገልጾ ከዚያ በፊት እጅግ ቢያንስ የማያጠራጥረው ደጋው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስለነበራት ግንኙነት አንድም ቃል አላሳረፈም። ጣልያን በመጀመሪያ አሰብን ይዞ ከዚያም ከአሥር ዓመታት በኋላ ወደ ምጽዋ መስፋፋቱን ኮሚሽኑ አልጠቀሰውም።

መግቢያው በመቀጠልም እ.አ.አ. በ1933 ዓ.ም የጣልያን ጦር ከኢትዮጵያ እንደተባረረ ሲገልጽ የኢትዮጵያ አርበኞች ጣልያኖችን በማባረር የተጫወቱት ሚና ከቶም አልተነሳም። እንዲሁም የእንግሊዝ ወታደሮችና የኢትዮጵያ አርበኞች ጣልያኖችን ካባረሩ በኋላ የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ኤርትራና ኢትዮጵያን አጣምሮ ያስተዳድር እንደነበረ ገልጾአል። ሆኖም እንደሚታወቀው ሁሉ እንግሊዞች በአገሪቱ አስተዳደር የተወሰነ ሚና ቢጫወቱም ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያንና ኤርትራን አጣምረው ያስተዳደሩበት ጊዜ የለም። ኮሚሽኑ ኢትዮጵያ እ.አ.ኣ. በሴፕቴምበር 1952 ዓ.ም የ1900፣ የ1902 እና የ1908 ዓ.ም. ውሎችን መሰረዝዋን ገልጾ፣ በተጨማሪም የኢትዮ-ኤርትራ ፌዴራል ሕገ መንግሥት ኢትዮጵያ ስለሰረዘችው በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የነበረውን ፌዴሬሽን ኢትዮጵያ አፈረሰችው ይላል። እስከ አሁን ባለው መረጃ ግን ፌዴሬሽኑ የፈረሰው በኢትዮጵያ ሳይሆን በኤርትራ ፓርላማ ሙሉ ድምጽ ነው። እዚህ ላይ በጣም የሚገርመው ኮሚሽኑ ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የጫነቻቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ሁለቱም ተዋዋዮች ሰርዘዋቸዋል ካለ በኋላ እንዴት ለውሳኔው መሠረት ሊያደርጋቸው እንዲቻለ ግር ይለል ውሎች ሁለቱም ተዋዋዮች ከሰረዙአቸው በኂላ መልሰው አድሰዋቸዋል የተባለበት ጊዜ የለም።

የኮሚሽኑ ሃተታ በመቀጠል እ.አ.አ. በሜይ 1998 ዓ.ም. በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ግጭት ተፈጠረ በማለት የአፍሪካ የዲፕሎማቶች ኮሚቴ ባድመና አካባቢውን ጉብኝቶ በአጠናቀረው ዘገባ ኤርትራ ወሰን ጥሳ ገብታ ወረራ እንደፈጸመች ቢያረጋግጥም ኮሚሽኑ ይህንን ሐቅ በማድበስበስ በሁለቱ አገሮች መሃከል ግጭት ተፈጠረ በማለት ያልፈዋል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የኮሚሽኑ ግድፈቶች ምናልባት ለመጨረሻም የፍርድ ውሳኔ የማጠቅሙም የሚጉዱም አይደሉም ቢባል እንኳን እጅግ ቢያንስ ኢትዮጵያ በጠበቆችዋ በአግባቡ እስመወከልዋን ይጠቁማሉ። የዚህ ችግር ምንጭ ምናልባትም እነዚህ ስህተቶች እንዲታረሙ የሚያሳስቡ ኢትዮጵያውያን የሕግ ባለሙያዎችና የታሪክ ምሁራን በቡድኑ አለመካተታቸው ነው። እነዚህ ኢትዮጵያን የወከሉ የውጭ አገር ዜጐች እንደዚህ ዓይነት ዝርዝር ሁኔታዎች እንዲያውቁም አይጠበቅባቸውም።

ኮሚሽኑ የቅኝ ግዛት ውሎቹ መሠረታዊ ጉድለት አላቸው ኢትዮጵያና ጣልያን ስለሰረዙአቸው በሥራ ላይ ሊውሉ አይችሉም በማለት ፈንታ በትርጉም ስም የወንዞችና የተራሮችን ስም እያስተካከለ፣ ተራሮችን ወደ አልተባለ ቦታ "እያንፏቀቀ" ወይንም ውሉ ባላስቀመጣቸው ቦታ እያስቀመጠ በመሠረቱ ውሎቹን እንደገና ጽፎአቸዋል በሚያሰኝ መልኩ ዋጋ እንዲኖራቸው አድርጉአል። ለምሳሌ "በለሳ" እና "ሙና" የሚባሉ ወንዞች ውሉ ሲፈረም እንዳልተጠቀሱ እየታወቀ ኮሚሽኑ ግን ለውሳኔው መሠረት አድርጎአቸዋል።

ግልጽ የሆነ የውል አንቀጽ በተዋዋዮቹ የቃል ስምምነት ብቻ ሳይሆን በድርጊትም ሊለወጥ እንደሚችልና ለውጡም ተቀባይነት እንደሚኖረው በግብጽና በእሥራኤል መሃከል በነበረው የድምበር ጉዳይ ተረጋግጦአል። በግብጽና በእሥራኤል መሃከል የተደረገው ውል በሁለቱ ድንበር ላይ ወሰናቸውን ለመለየት ትይዩ የሆኑ ምሰሶዎች ይተከላሉ ይላል። ከእነዚህ ምሰሶዎች አንዱ በትይዩ ሳይሆን ወጣ ብሎ ተተከለ። ግብጽም ሆነች እስራኤል ስህተቱን ለማረም ምንም ሳያደርጉ ቆይቶ ጭቅጭቅ ሲፈጠር ግብፅ ምሰሶው ትይዩ ሆኖ አልተተከለም፤ ስለዚህ ተቀባይነት



አይኖረውም ስትል ተከራከረች። ከመስመር ወጥቶ የተተከለው ምሰሶ አንዱ ወገን እንዲስተካከል ባለመጠየቁ የግልግል ዳኞች ግብፅ እንደተቀበለችው ይቆጠራል በማለት ወሰኑ[132]።

በተመሳሳይ መልኩ ባድመ በ1900 ዓ.ም. ውል መሠረት በኤርትራ ውስጥ ብትሆንም ለብዙ ዘመናት እንደ ኢትዮጵያ ግዛት ተቆጥራ ሕዝቡ ለኢትዮጵያ መንግሥት ቀረጥ ሲከፍል፤ በኢትዮጵያ መንግስት በተሾመ አስተዳዳሪ ሲተዳደር ሕዝቡ ተወካዮችን መርጦ ወደ ኢትዮጵያ ፓርላማ ሲልክ ኢትዮጵያ ግዛቴ ነው በማለት እነዚህን ሁሉ የሉዓላዊነት ተግባራት ስትፈፅም የጣልያን መንግሥትም ሆነ ኤርትራ ከተገነጠለች በኋላ አዲሱ የኤርትራ መንግሥት ተቃውሞ አሰምተው አያውቁም ነበር። ስለሆነም ኤርትራ አሁን ተነስታ ባድመ ሉዐላዊ ግዛቴ ነው ልትል አትችልም።

ሆኖም እነዚህን ሉዓላዊ መብቶች የሚገልጹ ተግባራት ኢትዮጵያ እየፈጸመች ሳለ ጣልያኖችም ሆኑ ኤርትራውያን ነፃ ከወጡ በኋላ ሳይቃወሙ በመቀጠላቸው ኮሚሽኑ ይህንን የሚገልጸው የህግ መርህ ኢፌክቲቪቴ (Effectivite') አልቀበልም በማለት ባድመን ለኤርትራ ሰጠ። አንድ አገር በአንድ ግዛት ላይ ግዛቱ ይገባኛል የሚለው አገር እያወቀ በይዞታው ያለው አገር የሉዓላዊነት ተግባራት ሳያቋርጥ እየፈጸመ ለብዙ ጊዜ የተባለው ግዛት በእጁ ያቆየው ከሆነ ይህ አገር ግዛቱን ለራሱ ሊያደርገው ይችላል የሚል የሕግ መርህ ኢፌክቲቪቴ (Effectivite') ይባላል[133]። የ1900 ዓ.ም የቅኝ ግዛት ውል መስመር ወደ ኤርትራ ቢያጥፈውም እንኳ ከላይ በተለገጸው የሕግ መርህ ምክንያት ባድመ ወደ ኢትዮጵያ መካለል ነበረበት። ሆኖም ኮሚሽኑ ኢፌክቲቪቴ የሚለው የሕግ መርህ ቢቀበልም ኢትዮጵያ ሉዐላዊነትን የሚያመላክቱ ተግባራት በቅጡ አስረድታ አሳማኝ ማስረጃዎችን አላቀረበችም በማለት ባድመን ወደ ኤርትራ አካለለ።

[132] See "Arbitral award in the Dispute Concerning certain Boundary Pillars between Arab Republic of Egypt and the State of Israe"l, 80 ilr 226 (27ilm 142 (1421) 1998.

[133] Malcolm Shaw supra note 69 ፑ፦ 140.

ምናልባትም ይህ ግልጽ የሆነ የሕግ መርህ ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ ያካከለው ኮሚሽኑ እንዳለው አንድም በኢትዮጵያ በኩል አሳማኝ ክርክርና በቂ ማስረጃ ባለማቅረቡ ወይንም ዳኞቹ ሆነ ብለው ለኤርትራ አዳሉ ማለት ይቻላል። በተጨማሪም ባድመ የጦርነቱ መንስኤ (Casus Belli) እንዳሆነችና ብዙ ኢትዮጲያውያን የተሰውበት መሆኑ ኮሚሽኑ ከግንዛቤ ሳያገባው አልፎታል።

ለኢሕአዴግ ደግሞ ይህ ውሳኔ እጅግ አሳፋሪና አሸማቃቂ እንደነበር ይባስ ብሎም ኮሚሽኑ ውሳኔውን ባስተላለፈ ማግስት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቀርበው "የጦር ሜዳው ድል በዓለም አቀፍ መድረክም ተደገመ፤ባድመ ለኢትዮጵያ ተፈርዶላታል፣ ባድመ የኢትዮጲያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋ ተረጋገጠ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደስ ይበልህ፤ደስታህን አደባባይ ወጥተህ ግለጽ" ማለታቸው ይታወሳል። ይኸ ደግሞ ሳይውል ሳያድር ፈጽሞ ሐሰት ሆኖ ባድመ ወደ ኤርትራ መታጠፉ ተረጋገጠ፤ ሃፍረቱ እጥፍ ድርብ የሚያደርገው ኢሕአዴግ በድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ኤርትራን አሸነፍን ከማለት ውጭ የኢትዮጲያ ሉዐላዊ ግዛት አሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍና የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት አንድም ቃል ትንፍሽ አላሉም።

ኢትዮጵያ በጦርነቱ ከአሸነፈች፥ በኋላ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መግለጫ በሰጡባቸው ጊዜያት ሁሉ በኢትዮጵያ በኩል የጦርነቱ ዋናው ዓላማ አቶ ኢሣያስን ሕግና ሥርዓትን ማስተማርና ሕገ ወጥነትን መቀልበስ እንጂ በኤርትራ የተያዙ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛቶችን ማስመለስ ነው ያሉበት አንድም ጊዜ የለም።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አባባል "ወረራውን የመመከት ጉዳይ የመሬት ጉዳይ አይደለም፤ የሕግ የበላይነት የሚያረጋግጥና አጉራ



ዘለልነትን የማስወገድ ጉዳይ ነው"[134] እንጂ በጠላት የተያዙ መሬቶች የማስመለስ ጉዳይ አይደለም።

ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ ምሁራን ያቀረቡለትን ሐሳብ አልቀበልም ያለው ኢሕአዴግ በመጨረሻ አልጀርስ ሄዶ አሳሪ ውል ፈርሞ ይግባኝ በሌለበት ግለሰቦች በሰጡት ውሳኔ ለመታሰር ፈቃደኛ መሆኑ ስህተት እንደሆነ የተረዳ ይመስላል። ምክንያቱም ኮሚሽኑ የሰጠው ይግባኝ ሊባልበት የማይቻለው ውሳኔ አክብሬ ፍርዱ የሚያዘውን እፈጽማለሁ ካለ በኋላ ቃሉን በማጠፍ አንድ ጊዜ በውሳኔው ላይ ማብራርያ ይሰጠኝ፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ጉዳዩ እንደገና በሦስተኛ አካል ይታይልኝ ማለቱ በውሳኔው አለመስማማቱን ይገልጻል። ዓለም በሙሉ በሚያውቀው የፍርድ ውሳኔ ላይ እንዲህ መዋዠቅ አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ኢሕዴግ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም እንደማያውቅ ወይንም ሆነ ብሎ ችላ ብሎት እንደነበር ያመለክታል።

[134] አብዮታዊ ዴሞክራሲ መጽሄት ግንቦት 1995

# ምዕራፍ 7

## 7. በድምበር ኮሚሽኑ ክርክር ኢትዮጵያን የወከለው ቡድን ለኤርትራ ያስረከባቸው የኢትዮጵያ መብቶች

በአልጀርስ የድምበር ኮሚሽን ክርክር ወቅት የኢትዮጵያ ተወካዮች ወይ ለክርክሩ ትኩረት ካለመስጠት ወይንም ደግሞ ሆነ ብሎ ኤርትራን ለመጥቀም በመፈለግ ወይንም በቀጣሪዎቻቸው በኢሕአዴግ ትዕዛዝ ኢትዮጵያን በግልጽ የሚጎዱ ውሳኔዎች በኢትዮጵያ ላይ እንዲወሰኑ የጠየቁባቸው ሁኔታዎች አሉ። እነዚህ ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች የድምበር ኮሚሽኑ ዳኞች አንዳንድ ክርክር የተነሳባቸው ቦታዎች ወደ ኢትዮጵያ ለማካለል በሚፈልጉበት ጊዜ እንኳን ሽንጣቸውን ገትረው ከዳኞቹ ጋር ክርክር ገጥመው አንዳንድ ቀበሌዎች ወደ ኤርትራ እንዲታጠፉ አድርገዋል።

### 7.1. በምስራቅ በኩል

#### ጠረፍ "Coast" ምን ማለት ነው?

የድምበር ኮሚሽኑ በተሰረዙና በሞቱ የቅኝ ግዛት ውሎች ላይ በመመሥረት የኢትዮጵያ የምስራቅ ወሰን ከጠረፍ ወደ ውስጥ በሚካለልበት ክርክር ጊዜ "ጠረፍ" (Coast) ከየት ይጀምራል የሚል ጥያቄ አንስቶ ነበር[135]።

[135] Eritrea-Ethiopia Boundary Commission Decision, Supra note 124 p.122.



ከ1908 ዓ.ም ውል በፊት አጼ ምኒልክ ከጣልያኑ ተወካይ ከሻለቃ ኔራዚኒ ጋር በተደራደሩበት ወቅት ወሰኑ ከጠረፍ ወደ ኢትዮጵያ ማለት ወደ ምዕራብ 60 ኪሎ ሜትር እንዲገባ ለሻለቃው ሃሳብ አቅርበውለት ይህ 60 ኪሎ ሜትር በሁለቱ ተዋዋዮች መካከል መግባቢያ ሆኖ ከ1897 ውሉ እስከ ተፈረመበት 1908 ዓ.ም ድረስ ወሰን ሆኖ አገልግሎአል[136]። በዚህ ውል ድምበሩ "ከጠረፉ" ይጀምራል ከማለት ሌላ ጠረፍ ከየት እንደሚጀምር "ጠረፍ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ አልተገለፀም ነበር።

የዚህ የ1908 ውል ስለጠረፍ የሚያወሳው አንቀፅ 1 የድምበር ኮሚሽኑ ዳኞች አንስተውት "ጠረፍ" ምን ማለት እንደሆነ ከየትስ እንደሚጀምር እንዲያስረዱ ባለጉዳዮቹን ጠየቁ። የድምበር ኮሚሽኑ ጥያቄውን በማብራራት "ጠረፍ" የሚለው የሚጀምረው ከደሴቶቹ ነው ወይስ ባሆሩ አልቆ በቀጣይነት ካለው መሬት ነው? የሚል ጥያቄ ለባለጉዳዮቹ አቀረቡላቸው።

የኤርትራ ተወካዮች የኢትዮጵያ ድንበር ከባህሩ ጠርዝ 60 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ ይገባል የሚለው፣ መሬቱ ከውሃ ጋር ከሚገጣጠምበት በቀጣይነት ወደ ውስጥ ማለት ወደ ምዕራብ ተለክቶ ነው እንጂ ከደሴቶች አይጀምርም ሲሉ ተከራከሩ። የኢትዮጵያ ተወካዮች በውሉ 60 ኪሎ ሜትር የተባለው የሚነሳው ከደሴቶቹ ጀምሮ ነው ብሎ ከመከራከር ፈንታ ከደሴቶቹ ሳይሆን ባህሩ ከመሬቱ ከሚገጣጠምበት ጀምሮ ነው በማለት ኤርትራ ከጠየቀችው ጋር በመስማማታቸው ኮሚሽኑ ወሰኑ የሚጀምረው ከደሴቶቹ ሳይሆን መሬቱ በቀጣይነት ከሚጀምርበት ነው በማለት በመሬቱና በደሴቶቹ መሃከል ያለውን እርቀት ለኤርትራ ሰጠ[137]።

ስለሆነም ከደሴቶቹ ጀምሮ ወደ ምዕራብ ቢለካ የኢትዮጵያ ድምበር እርቀቱ ከ60 ኪሎ ሜትር ትንሽ ያንሳል። አሁን በኤርትራ እጅ የወደቁ 160 ደሴቶች በቀይ ባህር ሲገኙ አንዳንዶቹ ከመሬቱ እርቀው የሚገኙ ናቸው።

[136] ዶ/ር ተወልደ ትኩእ ዝኒ ከማሁ 31 ገጽ 59

[137] Eritrea-Ethiopia Border Commission, supra, 124 p.123.

በኮሚሽኑ ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች የወሰዱት አቋም ከቶም ልክ ሊሆን እንደማይችል የህግ ሀሁ የቆጠረ ሰው ሊያውቀው የሚችል ነበር። ጣልያን ከኢትዮጵያ ጋር በ1908 ዓ.ም የፈረመችው ውልና ሌሎችም ኤርትራንና በአቅራቢያዋ የሚገኙት ደሴቶችን ቅኝ ግዛት ሲያደርጉ መሳውን ኤርትራ ማለት ደሴቶችንም ጨምሮ ነበር እንጂ ኤርትራን በከፊል አልነበረም። የኢትዮጵያ ተወካዮች "ጠረፍ" ማለት ምን ማለት ነው ከየትስ ይጀምራል ለሚለው ጥያቄ መልሱ እ.ኤ.አ. በ1982 ዓ.ም በወጣው የባህር በር ስምምነት (1982 Maritine Convention) በግልፅ ስለተቀመጠ ይህንን ፈልጎ ማግኘት አዳጋች አልነበረም። ይኸ ስምምነት አንድ ከባህር ጋር የሚዋሰን አገር ግዛቱ ከመሬቱ 12 ኖቲካ ማይልስ (Nautical miles) ወደ ባህሩ ዘልቆ እንደሚገባ ይገልፃል[138]። አሰብን የሚያካልለው ቀይ ባህር ከሚዶ ካሉት አረብ አገሮች በተለይም ከየመን ጋር የሚጋሩት በመሆኑ ባህሩ ለሁለት ተከፍሎ ግማሹ ወደ አፋር ግማሹ ወደ የመን መካለል ይኖርበታል። "ጠረፍ" የሚለው ከመሬቱ መጀመርያ ከሆነ ኤርትራ ከሚገባት ውጭ ቢያንስ ወደ ምዕራብ 12 ኪሎ ሜትር የኢትዮጵያን መሬት ይዛለች ማለት ነው።

"ጠረፍ" "coast" ማለት በደሴቶችና በመሬቱ መሃከል ያለው እርቀት ደሴቶችንም ይጨምራል። አጼ ሚኒልክ ተስማምተውበታል የተባለው 60 ኪሎሜትርም መለካት ያለበት ከደሴቶቹ ተነስቶ መሆን ይገባዋል በማለት ተከራክረው ኮሚሽኑ ውሳኔ ይሰጥበታል እንጂ ከኮሚሽኑ ውሳኔ በፊት የኢትዮጵያ ጠበቆች ቀድመው የኤርትራን ጥያቄ መቀበላቸው ማንን ይወክሉ ነበር የሚል ጥርጣሬ ያነሳል። አንድ ጠበቃ የወከለውን አካል ጥቅም ለማስጠበቅ ክርክሩን አቅርቦ ዳኝነቱን ለተመደቡት ዳኞች ይተዋል እንጂ እራሱ ዳኛ ሆኖ የተቃራኒውን ጥቅም አያራምድም። እንዲህ አይነቱ አሠራር ከጥብቅና ተግባር ውጪ ሲሆን ምናልባትም

[138] Hand book on the Delimitation of Maritime Boundaries, Division for Ocean Affairs and the Law of the Sea, office of Legal affairs, united nations, Newark, (2000) P.3



ጠበቃ ሆኖ ከመሠራት ሊያሣገድም የሚችል የስነ-ምግባር ጥሰትም ሊሆን ይችላል።

የድምበር ኮሚሽኑ ዳኞች "ጠረፍ" "coast" የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ መጠየቃቸው እራሱ ኤርትራን ለመጥቀም ተብሎ የተነሳ ጥያቄ ይመስላል። ዳኞች "ጠረፍ" "Coast" የሚለው ቃል ከደሴቶች ተነስቶ መለካት እንዳለበት ጠንቅቀው ያውቃሉ። አንድ ባህር የሚያዋስን አገር ግዛቱ እጅግ ቢያንስ 12 ኖቲካል ማይልስ ወደ ባህሩ ዘልቆ እንደሚገባ ወይንም ሁለቱ አገራት ትይዩ ከሆኑ ደግሞ በመሃከላቸው ያለው እርቀት ከ24 ኖቲካ ማይልስ ካነሰ ባህሩን እኩል እንደሚካፈሉት ዳኞች ሊያጡት አይችሉም።

## 7.2. ከአሰብ በስተ ምዕራብ ያለው ቡሬ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወሰን ሊሆን እንዴት ቻለ ?

ቡሬ በአሰብ መስመር የመንገድ ትራፊክ መቆጣጠሪያ መሆኑ ይታወቃል። ቡሬ ከባህሩ ጠረፍ ከ60 ኪሎ ሜትር ይበልጣል። በድምበር ኮሚሽኑ ክርክር ወቅት የኤርትራ ተወካዮች ቡሬ የኢትዮጵያና የኤርትራ ድምበር እንዲሆን ኢሕአዴግና ሻቢያ እንደተስማሙ ማስረጃ አቀረቡ።

ማስረጃውም "ከአዲስ አበባ እስከ መተሓለፊያ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ጥናት" ይላል። በዚህም ጥናት ላይ ተስማምተውበት ኢሕአዴግና ሻቢያ ተስማተውበት እ.ኤ.አ.በ1994 ፈርመውበታል።

ጥናቱ የትራንስፖርት የቁጥጥር ጣቢያዎችን ሲዘረዝር "ቡሬ የኢትዮጵያ ወሰን" "ቡሬ የኤርትራ ወሰን" ብሎ አስቀምጦታል። ስለሆነም ኮሚሽኑ ቡሬ የሁለቱም አገራት የወሰን ከተማ ነው ሲል ወሰነ። ይህም ማለት በቡሬ በኩል የጣልያኖች ውል ከመደበው ከ60 ኪሎ ሜትር በላይ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ዘልቃ ገብታለች ማለት ነው።

የድምበር ኮሚሽኑ ጥናቱ ለድንበር መካለስ ውሳኔ መሠረት ከማድረግ ፊንታ የጣልያን 60 ኪሎ ሜትር ስምምነት ማጽደቅ ነበረበት። አንድ ጥናት ሁለት ወገኖች በውል የተስማሙበትን ጉዳይ ሊሽር በፍጹም አይችልም። የድምበር ኮሚሽኑ ይህ ጥናት ተብየው ኢትዮጵያና ኤርትራ ሁለቱም ባለጉዳዮች የተስማሙበት አዲስ ውል ነው የሚል አቋም ነው የያዘው።

## 7.3. ምዕራብ ትግራይ

በምዕራብ በኩልም የተደረገው መካለል ኤርትራ ያነሳቻቸው አንዳንድ የይገባኛል ጥያቄዎች ኢትዮጵያ የበኩልዋን ክርክር አቅርባ ኮሚሽኑ ውሳኔ እንዲሰጥበት ከመተው ፊንታ የጥብቅና ሥርዓት በማይፈቅደው መንገድ የኢትዮጵያ ጠበቆች የኤርትራን ጥያቄ አምነው ተቀበሉ። በኮሚሽኑ ችሎት የኢትዮጵያ ወኪሎች የተጠቀሙችባቸው ቃላት እነዚህ ነበሩ።


"ፎርት ካርዶና፣ ሞኖክሲቶ፣ ጉና ጉና እና ጸረና የማያጠራጥሩ የኤርትራ ግዛቶች ናቸው።" ሞኖክሲቶና ጉና ጉናን የውሉ መስመር ኤርትራ ውስጥ ሲያደርጋቸው ለኮሚሽኑ የቀረቡት ማስረጃዎች ግን ጸረናና ፎርት ካርዶናን የውሉ መስመር ኤርትራ ውስጥ አያደርጋቸውም።

በተለይ ጸረናን በተመለከተ ኢትዮጵያ ለኮሚሽኑ ባቀረበችው ጽሑፍ ጸረና የኤርትራ ግዛት ነች በማለት ወደ ኤርትራ እንዲካለል የኢትዮጵያ ወኪሎች ኮሚሽኑን ጠየቁ።

ኮሚሽኑ ጸረና የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑን ተረድቶ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል በሚወስንበት ጊዜ የኢትዮጵያ ጠበቆች ጸረና የኤርትራ ሉዐላዊ ግዛት ነው ብለው ተከራከሩ።

ስለሆነም ኮሚሽኑ ይህንን ጸረና ወደ ኤርትራ ይታጠቃ የሚለው የኢትዮጵያ ጥያቄ ሊዘልለው ስላልቻለ ጸረናን ወደ ኤርትራ በማካለል የድምበሩ መስመር መለወጥ አስፈላጊ ሆኖአል ሲል ኮሚሽኑ ደመደመ። የድምበር ኮሚሽኑ ጸረናን ወደ ኤርትራ ለማካለል ሲል የድምበር መስመሩ ሃደቱን ቀይሮ ጸረናን እንዲሸፍን እንዴት እንዳጠረው ቀጥሎ ያለው ማፕ በግልጽ ያሳያል።

Map 11


International Boundary between the State of Eritrea and the Federal Democratic Republic of Ethiopia
CENTRAL SECTOR
Mercator Projection
Datum: WGS-84
Scale: 1:360,000
This map is produced for illustrative purposes only.
Reference Point
Eritrea-Ethiopia Boundary Commission
ERITREA
ETHIOPIA
ACCHELE GUZAI
SHIMEZANA
IROB
GULOMAKHEDA
AGAME
BADA
From the confluence of the Mereb and the Mai Ambessa to Point 11, the boundary follows the Mareb.
Senafe
Berachit
Guna Guna
Zalambessa
Alitena
Messolae
Rendacoma
Rogali
Adigrat
Debre Damo
Fort Cadorna
Kollobenda
Belesa
Belesa C
Endeli
Muna / Berbero Gado
Salt Lake
11
12
13
14
15
16
17
18
20
21
22
23
24
25
26
27
28
29
30
31
40°00'
40°15'

ኮሚሽኑ ውስ የሚደነግገውን ግልጽ የድምበር መስመር አክብሮ ውሳኔ መስጠት እንጂ፣ ክርክር ያልተነሳበትን ጉዳይ የድምበር ኮሚሽኑ በራሱ ተነሳሽነት ማስተናገድ አይገባውም ነበር። ኮሚሽኑ ምንም ያላከራከረው ጾረና ወደ ኢትዮጵያ መካለል ይገባው ነበር ወይንም አይገባውም ብሎ መጠየቅ ተገቢ አልነበረም። አንድ ዳኛ አንድን የውል አንቀጽ ወይንም ክፍል አሻሚ ከሆነበት ወይንም ግልጽ ካልሆነለት የሁለቱም ወገኖች ጠበቆችን የየበኩላቸው አቋም ጠይቆ ዳኛው ከብዙ ዓይነት የትርጉም ስልቶች በአንዱ ተጠቅሞ አንቀጹን ሊተረጉም ይችላል። ይህ ጾረና ወደ ኢትዮጵያ የሚያጥፈው የውስ አንቀጽ ግልጽ ስለነበር ውስ የሚለውን በቀጥታ ማስፈፀም እንጂ መተርጉም ወይንም ሌላ ጥያቄ ማስተናገድ አልነበረምበትም። ኢትዮጵያ ብትፋልግ ከኮሚሽኑ ውጭ ጾረናን ለኤርትር ትስጥ እንጂ በዚህ ግልፅ በሆነ ነገር ኮሚሽኑ የኢትዮጵያ ጠበቆች ጥያቄ ማድመጥ አስፋላጊ አልነበረም። በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ተወካዮች መቀሌንም ለኤርትር ይስጥ ብለው ቢጠይቁ ኮሚሽኑ ሊቀበል ነው ማለት ነው? እንዲያውም የኢትዮጵያ ተወካዮች የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት ለኤርትራ ይስጥ በሚሉበት ጊዜ ድርጊቱ የጥብቅናን ሥነ-ምግባር የሚጥስ ተግባር እንደመሆኑ መጠን ኮሚሽኑ ጉዳዩ መመርምር ይገባው ነበር። ምክንያቱም አንድ ጠበቃ አላፊነቱ የቀጠረው የደምበኛውን ጥቅሙን ወይንም መብቱን ማስከበር እንጂ ለባላጋራው እንዲሰጥበት አይደለም።

ይህ የድምበር ኮሚሽን የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑ ያወቀላትን የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት ለሌላ አገር አሳልፎ መስጠት ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች ውሳኔ ብቻ ሊሆን አይችልም። ጠበቆቹን የቀጠረው የኢሕአዴግ መንግሥት መመርያ ተከትለው መሆን አለበት። ይህ ጾርና በስጦታ ለኤርትራ የተሰጠው በጠበቆቹ ውሳኔ ከሆነ ኢትዮጵያ ጠበቆችዋን ማባረርና ጉዳዩን ለኮሚሽኑ ማቅረብና ማስመርመር ይገባት ነበር። በኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት ትዕዛዝም ከሆነ ይህንን የኢትዮጵያ

ሉዐላዊ ግዛትን አሳልፎ ለሌላ መስጠት በሕግም ሊያስጠይቅ ይችላል።

ይህንን የመሰለ ከጥብቅና ሙያ ስነ ምግባር ውጭ የሆነ ድርጊት ጠበቆች በራሳቸው ተነሳሽነት ያደርጉታል ለማለት ይቸግራል። ጉዳዩ ከፍተኛ ኃላፊነት የሚያስከትል ስለሆነ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛት ለጠላት አሳልፎ ማን እንደሰጠ ተጣርቶ ውሳኔ በሰጠው ሰው ላይ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ የግድ ይላል። ከእነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች ሌሎችም ኢትዮጵያን የጐዱ ስህተቶች እንዳሉ ማስታወስ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ከዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር[139] በላይ ከፍላ የቀጠረቻቸው ጠበቆች ጾረናን ኮሚሽኑ ከወሰነው በተቃራኒ ለኤርትራ አሳልፈው ሲሰጡ "በቆረጥከው ዱላ ብትመታ፣ በመረጥከው ዳኛ ብትረታ" መገረም የለብህም የሚለው የአበው አባባል ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ ደረሰ።

## 7.4. የደብር ቢዘን ገዳም

በምጽዋ መንገድ ከአሥመራ ትንሽ ወጣ ብላ የምትገኝ ጥንታዊት ገዳም ነች። ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር የቆየ ትስስር ስላላት እ.አ.አ ግንቦት 2ቀን በ1889 ዓ.ም በኢትዮጵያና በጣልያን በተፈረመው በውጫሌው ውል በአንቀጽ 4 ገዳሚቱ እስከ ምጽዋ ከሚደርሰው እርስተ ጉልትዋ ጋር የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት ሆና እንደትቆይ ስምምነት ተደርሶ ነበር። በተጨማሪም ደብረ ቢዘን ገዳምን በምንም ዓይነት መልኩ ኢትዮጵያ ለወታደሪዊ ጥቅም እንዳታውለው ውሉ ይከለክላል።

የአልጀርስ ስምምነትም ሆነ የድምበር ኮሚሽኑ ስለዚህ ስምምነት ምንም ያሉት ነገር የለም። በድምበር ኮሚሽኑ ፊት ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆችም ስለደብረ ቢዘን ምንም ያመለከቱት ነገር አልነበረም።

በእርግጥም ኤርትራ ውስጥ የምትገኝ አንዲት ገዳም ኤርትራ ነፃነትዋ ስትጐናጸፍ ገዳምዋ የኢትዮጵያ ግዛት ሆና የምትቆይበት መንገድ የለም። ሆኖም ግን አማራጩ በገዳሙ ምትክ ኤርትራና ኢትዮጵያ ተደራድረው ለኢትዮጵያ ማካካሻ መስጠት ፍትሐዊ አካሄድ በሆነ ነበር። አለፍ ቀደም ቢል የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋ ቢረጋገጥም ለሰላምና ለመልካም ጉርብትና ሲባል ለደብር ቢዘን ማካካሻ ብትሆን ለሁለቱም አገር ሰላም ጥሩ መፍትሔ ነበር ሆኖም በተደጋጋሚ እንደታየው ኢትዮጵያን የሚወክሉ ጠበቆች አሁንም የኢትዮጵያ መብት አሳልፈው ሰጥተዋል።

በተመሳሳይ መልኩ የአልጀርስ ስምምነትም ሆነ የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ እ.አ.አ በ1900 በተፈረመው ውል የተደነገገው ጣልያን በማንኛውም ምክንያት ኤርትራን ለቅቃ ብትወጣ መሬዋ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ትታጠፉለች የሚለውን አንቀጽ የኢትዮጵያ ጠበቆች ሳያነሱት በዝምታ አልፈውታል። ይህም ማለት የድምበር ኮሚሽኑም ሆነ ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች ሆነ ብለው ኢትዮጵያን የሚጐዱ አንቀጾችን ነቅሰው አውጥተው ተፈጻሚ ሲያደርጉ ለኢትዮጵያ አንዳንድ መብቶችን የሚያጐናጽፉ አንቀጾችን ደግሞ ሆነ ብለው ሲዘልሉአቸው በተደጋጋሚ ተስተውሉአል።

## 7.5. የህግ አመራረጥ

ከላይ እ፡ደተገለጸው የድምበር ኮሚሽኑ ለውሳኔው መሠረት ያደረጋቸው ጣልያንና ኢትዮጵ፡ "የተስማሙባቸው" የቅኝ ግዛት ውሎች ሆነው በተጨማሪም አግባባነት ያላቸው የዓለም አቀፍ ሕጎችንና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የ1964 ዓ.ም የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ እንዲሆኑ የኢትዮጵያ ተወካዮች መስማማታቸው ይታወሳል። የኢትዮጵያ ተወካዮች ጣልያን ለጥቅሟ ስትል በኢትዮጵያ ላይ በግድ የጫነቻቸው ውሎች ለኢትዮጵያ

[139] ኢትዮጵያ ለድምበር ኮሚሽኑ ሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን ዶለር መክፈልዋን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ይገልጻሉ። ኢትዮጵያ የባህር በርዋን አሰብን ለኤርትራ ለመስጠት ጾረናና ባድመንና ሌሎችም ግዛቶችዋን በፍርድ ለኤርትራ ለማስረከብ ዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር ወጪ አስወጥቶአታል

ይጠቅማሉ ብለው በዚህ መስማማት "አይናችሁን ጨፍኑ እናሞኛችሁ" ዓይነት ነው። ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች እነዚህ የቅኝ ግዛት ውሉች ደንበኞቻውን ኢትዮጵያ የሚጎዱ መሆናቸው ለደንበኞቻቸው ለኢትዮጵያ መንግሥት ማስታወቅ የጥብቅና ተግባር የሚጠይቀው ሃለፊነት ነበር። ይህንን ካላስታወቁ የጥብቅና ሥነ ምግባር ጥሰዋል።

ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ በእነዚህ በተሻሩ ውሉች ይመርኮዝ ከማለት ይልቅ የዓለም ሕብረተሰብ የሚጠቀምባቸውና ከዚህ በፊትም የተጠቀመባቸው የተፈተኑ የዓለም አቀፍ ህግጋት፣ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ውሳኔዎች፣ የታወቁ ምሁራን ትንታኔዎች ወዘተ.....ፍትሕን ለማስፈን ይበልጥ ይጠቅሙ እንደነበር መገንዘብ ይገባቸው ነበር። ውሳኔዎቹ በቅኝ ግዛት ውሉች ይመሥረቱ ብሉ ክርክር ማቅረብ ሌላውን ወገን ለመጥቀም ታስቦ ካልሆነ በስተቀር እንዴት እንዲህ ዓይነት በኢትዮጵያ ላይ በግድ የተጫኑ ውሎች ደንበኞችን ይጠቅማሉ፣ፍትሕ ያሰፍናሉ ተብሉ ይታሰባል? ደንበኞቸው ኢሕአዴግም የኮሚሽኑ ውሳኔ እነዚሁ በፈረሱ የቅኝ ግዛት ውሉች መመሥረት አለበት ብሉ ድርቅ ካለም ጠበቆቹ ሥራውን ትተው መሰናበት ይገባቸው ነበር እንጂ ሕገ ወጥ በሆኑ "ውሉች" ተመርኩዘው በመከራከር የሕዝብን መብቶች ማስረከብ አይገባቸውም ነበር።

## 7.6. ሁለት ወዶ አይሆንም

የድምበር ኮሚሽኑ ለውሳኔው መሠረት ካደረጋቸው ሕጎች በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባኤ በካይሮ በ1964 ዓ.ም በውሳኔ ቁ AHG/Res 161(1) የተደነገገው አንዱ ነበር። ይህም ውሳኔ ቅኝ ግዛት የነበሩ አገራት ነፃ በሚወጡበት ጊዜ በቅኝ ግዛት ወቅት የነበረውን ወሰን (ድንበር) ማክበር እንዳለባቸው ይደነግጋል[140]።

---

[140] የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ቁ ውሳኔ AHG/Res 16(1)



በመጀመሪያ ደረጃ ኤርትራ ከቅኝ ግዛት ነጻ የወጣችው በ1952 ዓ.ም በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ስትቀላቀል ሲሆን ኤርትራ ከኢትዮጵያ በተገነጠለች ጊዜ በሁለቱ አገራት የነበረው ግንኙነት የቅኝ ገዢና ተገዢ አልነበረም። ስለሆነም ይህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ወሰን መካለል አግባብነት የለውም።

ይህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባኤ ውሳኔ ከቅኝ ግዛት ነፃ ለሚወጡትና በተጨማሪም ለሌሉች በመገንጠልም ይሁን ወይንም በሌላ መንገድ ነፃነት ለሚጎናጸፉ አገራት አግባብነት አለው ከተባለ ኤርትራ ነፃ ስትወጣ የነበራትን ግዛት ይዛ ትሄዳለች እንጂ ነፃ በወጣች ጊዜ በግዛትዋ ውስጥ ያልነበረውን አሰብን ልትወስድ አትችልም። ይህ እጅግም አስቸጋሪ ያልሆነ ግልፅ የህግ ነጥብ የኢትጵያ ተወካዮች እንዴት ዘነጉት? ጉዳዩ የዝንጋታ ሳይሆን የሌላ ይመስላል።

ስለሆነም ኤርትራውያን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበርን ካሉ ነፃ ሲወጡ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ትተው የያዙትን መሬት ብቻ ይዘው ይገነጠላሉ። የለም የኢትዮጵያ አካል እንጂ ቅኝ ግዛት አልነበረንም ካሉም ደግሞ ሊገነጠሉ የሚችሉት አንዳንድ ግዴታዎችን ካሟሉ በኂላ ብቻ ነበር።

## 7.8. "በያዝከው እርጋ" (UTI POSSIDETIS JURIS)

በቅኝ ግዛት ስር የነበረ አንድ አገር ነፃ በሚወጣበት ጊዜ ወሰኑ የትኛው መሆን አለበት የሚለው ጥያቄ በመጀመርያ የተነሳው በ19ኛው ምዕተ ዓመት የስፔን ቅኝ ግዛት የነበሩ የላቲን አሜሪካ አገራት ነፃ በወጡበት ጊዜ ነው። እነዚህ የቀድሞ የስፔን ቅኝ ግዛቶች ነፃ ሲወጡ ወሰናቸው ቅኝ ገዢዋ ስፔን የመሰረተቻቸው ድንበሮች መሆን አለበት ተብሉ "በያዝከው እርጋ" UTI POSSEDETIS የሚል አንድ የሕግ መርህ ተፈጠረ። ይህ መርህ ይበልጥ ጉልቶ የወጣው የአፍሪካ አገራት ከቅኝ ግዛትነት ነፃ ሲወጡ ወሰናቸዉ የትኛው መሆን አለበት ለሚለው ጥያቄ፣ በ1964 ዓ.ም. በካይሮ. ተሰብስቦ የነበረው የአፍሪካ አንድነት የመሪዎች ጉባዔ ይህንኑ መርህ ተቀብሉ አንድ አገር

ነፃ በሚወጣበት ጊዜ ቅኝ ገገርዎች የመሠረቱት አንድ ቋሚ ወሰን ስላለው ያ ወሰን ሳይለወጥ የአዲሲቱ አገር ድምበር እንዲሆን ተወሰነ::[141]

ይህንኑ ውሳኔ በማጽደቅ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል አገራት ነፃ የቅኝ ግዛት ወሰኖችን ላለመለወጥ ቃል ገቡ። ይህንን መርህ በመጣስ በቤልጂያን ኮንጐ፣ በናይጀርያና በሱዳን ከግዛቶቻቸው ውስጥ አንዳንዶቹ ክፍሎች የቅኝ ግዛት ወሰኖችን በመለወጥ ሊገነጠሉ በሞከሩ ጊዜ በአፍሪካ አገራት ተቃውሞ ገጠማቸው[142]::

ይህ "ብያዝከው እርጋ" የሚለው የሕግ መርህ በሂደት ተስፋፍቶ የሚመለከተው ከቅኝ ግዛት ነፃ የወጡ አገሮች ብቻ ሳይሆን በማንኛውም መንገድ ለምሳሌ በአገሪቱ መከፋፈል ተፈጥሮ ነፃ ለሚወጡ አገራት አግባብነት እንዲኖረው ሆኖአል። ነፃ የወጣው አገር ወሰኑ በውስጥ አስተዳደር የተመሠረተ ወይንም የቅኝ ግዛት ወሰን ሊሆን ይችላል። አዲሱ አገር ነፃ በሚወጣበት ወይንም በሚገነጠልበት ጊዜ ያ የአስተዳደር ወይንም የቅኝ ግዛት ወሰን በዚህ የህግ መርህ መሠረት የጸና ይሆናል ማለት ነው።

ሥርቶ አደሩ ሕዝብ የራሱን ዕድል በረሱ ለመወሰን እንዲችል የብሔረሰቦች እኩልነት ለማረጋገጥ የአካባቢው የራስ በራስ አስተዳደርን ተግባሪዊ ለማድረግ የልማት ተግባሮችን ለማከናወን የአካባቢው ብሔረሰቦች ቋንቋ እንዲደብሩ እንዲስፋፋና በጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሲባል የትግራይ፣የአሰብ፣የድሬዳዋና የኦጋዴን ክፍለ ግዛቶች በአዋጅ ቁ. 16/1980 ዓ.ም ራስ ገዝ ተብለው ተቋቋሙ እነዚህ ክልሎች የራሳቸው ወሰን ያላቸው[143]:: የኢትዮጵያ የውስጥ አስተዳደር ወሰን መለወጥ ሉዓላዊ መብቷ ሲሆን እነዚህ ራስ ገዝ አስተዳደሮች ወይንም ክልሎች የራሳቸው ወሰን ከመሠረቱ ከአሥር ዓመታት በላይ ሲሆን እነዚህ ወሰኖች የረጉ መሬት የጨበጡ ሆነው ነበር::

ኤርትራ ነፃነትዋን በተጐናጸፈች ጊዜ ይህ ጸንቶ የቆየው ኤርትራንና አሰብን የሚለየው የአስተዳደር ወሰን ጥሳ በጊዜው የኤርትራ አካል ያልነበረችውን አሰብን ስትይዝ ክልካይ

[141] ዝኒ ከማሁ.

[142] Malcolm Shaw, Supra note 69. P. 447.

[143] የትግራይ፣የአሰብ፣ የድሬዳዋና የኦጋዴን ራስ ገዝ አካባቢዎች ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁ.16/1980 ዓ.ም.



አልነበረባትም ። በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ያለውና የነበረው የወሰን ሁኔታ በሶቭየት ሕብረት በዩጐዝላቪያና በቼኮስሎቫቢያ ከተከሰተው ጋር ይመሳሰላል። ሶቭየት ሕብረት ፈርሳ የህብረቱ አባል የነበሩ አገራት ተከፋፍለው ነፃ በወጡበት ጊዜ ቀደም ሲል ሶቪየት ህብረት መስርቶት የነበረው ወሰን ተከትለው ነፃ ወጡ። እንዲሁም ዮጐዝላቪያ ስትከፋፈል ቀደም ሲል በዮጐዝላቪያ አስተዳደር የተመሠረቱ ድምበሮች እንደጸኑ ሆነው ሰርቢያ፣ ክሮሲጐቪ፣ ክሮዌሽያና ሞንቲኔግሮ ሲለያዩ የቀድሞውን ድምበሮቻቸው አልለወጡም። ሞንቲኔግሮ ቀደም ሲል ግዛትዋ ያልነበረውን ክፍል ከሰርቢያም ሆነ ከሌሎቹ አልጠየቀችም::

በአጠቃላይ ዩጐዝላቪያ በመባል ይታወቁ የነበሩ አያሌ አገራት ወይንም ክልሎች ነፃ በወጡበት ጊዜ የነበረውን ድምበር ጥሰው የሌላውን ግዛት የያዙበት ሁኔታ አልነበረም። ዩጐዝላቪያ በተበታተኑቹ ጊዜ የግዛቶቹ ወይንም የክልለሎቹ ወሰን እንዲያካልል የተቋቋመው የግልግል ኮሚሽን (Arbitration Commission) "ሁኔታ ምንም ይሁን ምንም የራስን ዕድል በራስ መወሰን በጊዜው የነበሩ ወሰኖችን ሊለውጥ አይችልም።"[144] ብሎ ውሳኔ ሰጠ። ይህ መርህ በጊዜው ያለው ድምበር እንዴት ተፈጠረ ሳይባል የተረጋጋውንና መሬት ላይ ያለውን ማጽደቅ እንደሚገባ የዓለም አቀፍ ሕግ ያስገነዝባል። ስለዚህ ኤርትራ ከአሰብ ጋር የነበራትን ወሰን ጥሳ አሰብን ስትይዝ በሁለት መንገዶች የዓለም አቀፍ ሕግን ጥሳለች ማለት ነው።

ሕወሓትና ሻቢያ በዚህ ጉዳይ አስተሳሰባቸው የጨቅላ ቢሆንም ኤርትራን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት በመሆንዋ ነፃ መውጣት ይገባታል በማለት ለዚህም እኩይ ዓላማቸው ስኬታማነት ብዙ ዋጋ ከፍለው ኤርትራ ነፃ ወጣች ወይንም ከኢትዮጵያ ተገነጠለች። እንግዲህ ኤርትራ ከኢትዮጵያ "ቅኝ ተገዢነት" ነፃ ስትወጣ ቅኝ ግዛት የነበሩ አገራት ነጻ በሚወጡባት ጊዜ በወቅቱ የነበራቸው ግዛት የቅኝ ግዛቱ ወሰን ሳይለውጡ ነፃነታቸውን እንደሚጎናፀፉና ይህም የህግ መርህ በካይሮ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ጸድቆ በአፍሪካ ተፈጻሚነት አግኝቶ የአለም አቀፍ ሕግ አካል ሆኖአል። ስለዚህ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነፃ ስትወጣ "የኢትዮጵያ ቅኝ

[144] Shaw, Malcalm supra, note 69. p 447.

ግዛት" በነበረችበት ጊዜ አሰብ ራስ ገዝ እንጂ የኤርትራ አካል አልነበረችም። ስለሆነም ኤርትራ ነፃ ስትወጣ የአሰብን ራስ ገዝ ሳይጨምር ከአሰብ ራስ ገዝ ሰሜን የሚገኘውን አገር ይዛ መሄድ ይገባት ነበር። ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ የዓለም አቀፍ ሕግ አካል የሆነውን የ1964 ዓ.ም. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔን ጥሳ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት አሰብ ራስ ገዝን ይዛለች ማለት ነው።

ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ከተባለ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነፃ ስትወጣ የኢትዮጵያ የውስጥ አስተዳደር ድምበሮችን ማክበር ይኖርባት ነበር። ይኸም ማለት ራስ ገዝ በነበረችው በኤርትራና በሌላዋ ራስ ገዝ በአሰብ መሃከል የነበረው ኢትዮጵያ መሠርቶት የነበረው ድምበርን ኤርትራ ማክበር ነበረባት። ኤርትራ ይህ ከአሰብ ጋር የሚለያትን ወሰን ጥሳ አሰብን ጠቀለለች። ይህ ኤርትራ የፈጸመችው ጥሰት "በያዝከው እርጋ" <u>(UTI POSSIDETIS)</u> የሚደነግገውን የሕግ መርህንና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የ1964 ዓ.ም የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔን ይሽራል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት የህግ መርሆች ማለት የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የካይሮ ውሳኔና "በያዝከው እርጋ" የሚለው መርህ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው ስንል እውነትም ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ወይንም ነበረች የሚለውን አምነን ተቀብለነው ሳይሆን ሻቢያና ሓወሓት/ኢሕአዴግ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ካሉ ውጤቱን በፀጋ መቀበል ነበረባቸው ለማለት ነው።

እነዚህን ሁለት የሕግ ጥሰቶችንና የአሰብ እራስ ገዝ በኤርትራ መነጠቅን በድምበር ኮሚሽኑ ችሎት ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች አላነሱትም። ምናልባት አሰብ የኢትጵያ አካል ነች ብሎ መከራከር የአሰብ ኢትዮጵያዊነት በተነሳ ቁጥር በቁጣ የሚገነፍሉ አንዳንድ ኢሕአዴጐችን ስለሚያስከፋ ሆነ ብለው ዘልለውት ወይንም በክርክሩን ውቅት ነጥቡን እንዳያነሱ መመርያ ተሰጥቶአቸው ሊሆን ይችላል።

የኢትዮጵያን ጥቅም ተከታትሎ የሚያስጠብቅ አካል ቢኖርና ይህ ምናልባት አዋጪ ሊሆን ይችል የነበረ ክርክር ለድምበር ኮሚሽኑ ቢቀርብ ምናልባትም አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛትና የባህር በር ሆና ልትቀርና የቀይ ባህር አፋሮችም አንድነትና ኢትዮጵያዊነት ሊከበርላቸው በተቻለ ነበር። ይህን አብይ የሕግ ክርክር በድምበር ኮሚሽኑ ችሎት አለማንሳት አሁንም የኢትዮጵያ መብት አሳልፎ መስጠት ነው።

የድምበር ኮሚሽኑ ዳኞች ይህን የመሰለ የሕግ መፈናፈኛ ቢቀርብላቸው ኖሮ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ዓለም የደገፈው ጉዳይ ስለነበርና 90 ሚልዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ በእግር መንገድ እርቀት ወደብ አልባ ማድረግ ፍጹም ኢፍትሐዊ ስለሆነ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲታጠፍ ዳኞቹ ሊወስኑ ይችሉ ነበር፡

## 7.9. የድምበር ኮሚሽኑ መሬታቸውን ወደ ኤርትራ ያካለለባቸው ኢትዮጵያውያን የዜግነት መብት

በአልጀርስ ስምምነት የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ኮሚሽን የሞቱ የቅኝ ግዛት ውሎችን ከመቃብር ቆፍሮ አውጥቶ በሥራ ላይ አውሎ በሰጠው ውሳኔ መሰረት የቀይ ባህር አፋርን በከፊል ኢሮብን ኩናማንና ጾረናን ለኤርትራ መስጠቱ ከዚህ በላይ በዝርዝር ተገልፀአል።

የድምበር ኮሚሽኑ እነዚህን አካባቢዎች ለኤርትራ ሲሰጥ በቦታው ነዋሪ የሆነውን ሕዝብ ታሪክ መመዝገብ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የያዘውንና እትብቱ የተቀበረበትን መሬት ነዋቆ ኢትዮጵያዊነት ዜግነቱን ገፍፎ ኮሚሽኑ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ሕዝቡን ኤርትራዊ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለህም ብሎታል። እነዚህ ኢትዮጵያውያን ከአያት ከቅድመ አያቶቻቸው ከዚያም በፊት የቀድሞዎቹ የጠላት ወረራዎችንና የቅርብ የሻቢያንም ጭምር ሲመክቱ ኖረዋል። በአድዋ ጦርነት ጣልያንን ካምበረከከው የኢትዮጵያ ጦር ውስጥ የአፋር ደግኖች ጉልህ ሚና እንደተጫወቱ አዛገርቸው ልዑል ራስ መኰንን በሕይወት ቢኖሩ በመሰከሩላቸው። የኢሮብም ሕዝብ የጣልያኖች ቅኝ ግዛት ከነበረችው ኤርትራ ጋር ስለሚጐራበት ዘወትር የወራሪዎቹ ገፈት ቀማሽ ሆኖ (የሻቢያንም ጭምር) ለአገሩ ነፃነት ብዙ መስዋትነት የከፈለ ሕዝብ ነው።

ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ቅንጣት ያህል እውቀት የሌላቸውና ስለኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና የባህር በር መከበር ጉዳያቸው ያልሆነው ፈረንጆችና አንድ አፍሪቃዊ፣ ዛሬ ተነስተው የኢሮብን፣የአፋርንና የኩናማን ሕዝብ ኤርትራዊ ነህ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለህም ብለውታል። ስለሆነም ወሰኑ በሚካለልበት ጊዜ እነዚህ ኢትዮጵያውያኑ ያላቸው አማራጭ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው ይዘው ወደ መሃል ኢትዮጵያ አገር ይሰደዳሉ፣ ወይንም የሻቢያ መልካም ፈቃድ ከሆነ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን እንደያዙ የኤርትራ ፖስፖርት አውጥተው በኤርትራ ውስጥ እንነደውጭ አገር ዜጋ በመሬታቸው ላይ ሊኖሩ ይችላሉ።

ይህም የኤርትራ መንግሥት ፈቃድ ከሆነ ነው እንጂ የኤርትራ መንግሥት የእነዚህ ኢትዮጵያውያን የጸጉር አቁራረጥ ካላስደሰተው ከነበሩበት አስነስቶ ኤርትራ ውስጥ ሌላ ቦታ ቢያስፍራቸው ሉዐላዊ መብቱ ነው።

ይህ ኢትዮጳያውያን ዜግነታቸውን ጥለው የኤርትራ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስገድደው የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ "የሰብአዊ ሁሉ አቀፍ መብት መግለጫ" (Declaration of Human Rights) አንቀጽ 15ን በግልጽ ይጥሳል። ይህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 1 "ማንም ሰው የዜግነት መብቶቹ በዘፈቀደ አይገፈፍም" በማለት ይደነግጋል። ይህንን መሠረታዊ መብት በሌሎች የሰበአዊ መብት ሰነዶችም ሰፍሮአል። በ1948 ዓ.ም. የወጣው የላቲን አሜሪካና የሰሜን አሜሪካ የሰው ልጆች መብት መግለጫ (American Declaration of the Rights of Man) "ማንኛውም ሰው ሕግ የሚያጐናጽፈው ዜግነት እንዲኖረው መብቱ ነው። ዜግነቱን የሌላ አገር ዜግነት ሊሰጠው ፈቃደኛ በሆነ አገር ዜግነት ሊለውጠው" እንደሚችል መግለጫው ይደነግጋል። የአንድ ሰው የዜግነት መብት በዓለም አቀፍ ሕግ የተከበረና በጣምም ዋጋ ያለው መብት ለመሆኑ እነዚህ ሕግጋትና ሌሎችም ያመለክታሉ።

የኢሮብ ሕዝብ በተደጋጋሚ ኤርትራዊ እንዳልሆነና ለኢትዮጳያዊ ዜግነቱ እስከ ሞት እንደሚታገል በተለያዩ ጊዜአት አስታውቆአል። እ.ኤ.አ. ፌብርዋሪ 8 ቀን 2002 ዓ.ም. "የዛላምበሳና ኢሮብ አካባቢ ኮሚቴ" በሚል ስያሜ የተቋቋመ ቡድን ለተባበሩት መንግሥት ድርጅትና የአልጀርስ ስምምነት በማስፈፀም ተሳታፊ ለሆኑት መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መሬታቸው ወደ



ኤርትራ እንዳይከለልባቸውና ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው እንዲከበርላቸው ተማጽነዋል። እንዲሁም በኤርትራ ወረራ መሬታቸው በተያዘበት ወቅት በኤርትራ ሠራዊት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ የኢሮብ ተወላጆች ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ እንዲደረግ ኮሚቴው ቀይ መስቀል ማህበርን ጠይቋል[145]።

ኢሕአዴግ አልጀርስ ላይ በተፈራረመው ውል ኢትዮጵያና ኤርትራ ወሰን በሚከለሉበት ወቅት ሁለቱም አገራት በበኩላቸው በየጠረፋቸው ጸጥታውን እንዲያስጠብቁ ተስማምተዋል ። የኢሮብ ሕዝብ ደግሞ መሬቱንና ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን በምንም ዓይነት እንደማይለቅ ለዚህም መብቱ ለመሞት ዝግጁ መሆኑን በተለያዩ ጊዜአት አስታውቆአል። ድንበር በሚከለልበት ወቅት የኢሮብ ሕዝብ በዚሁ አቋሙ ቢጸና መንግሥት ምን ሊያደርግ ነው? የጸጥታ አስከባሪ ኃይሎች ፈረንጆች አለአግባብ የሰጡትን ውሳኔ ለማስፈጸም በገዛ ሕዝቡ ላይ እንደማይተኩስ እንተማመናለን። የድምበር ኮሚሽኑ ወደ ኤርትራ ባጠፋቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የኢሮብና የዛላምበሳ፣ የአፋርና የኩናማ ሕዝቦች ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው ከመገፈፉ በፊት ኤርትራዊነት ወይንም የኢትዮጵያ ዜግነት ይመርጡ እንደሆነ በሕዝብ ውሳኔ ማረጋገጥም በተቻለ ነበር። ያም ሆነ ይህ ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች ይህንን ግልጽ የሆነ የሕግ መርህ በክርክራቸው ወቅት አላነሱትም። ስለሆነም ይህን ክርክር በድምበር ኮሚሽኑ ፊት አለማቅረባቸው ሌላው የኢትዮጵያ መብት ለኤርትር አሳልፎ እንደመስጠት ይቆጠራል።

## 7.10. ከጦርነቱን በፊትም ሆነ በኋላ አሰብን ማስመለስ የሚያስችሉ የነበሩ ሁኔታዎች

የኤርትራ ጦር ጥቃቱን የሰነዘረውና ባድመንና አካባቢውን የያዘው አንዳንድ የፖለቲካ መሪዎች ኤርትራ ለጦርነቱ ዝግጅት እያደረገች መሆኑ የሚያረጋግጡ አንዳንድ ማስረጃዎች

[145] "ከዛላምበሳ ኢሮብ ቀጣና ጊዜያዊ ኮሚቴ የቀረበ የምድረ ኢሮብ አቤቱታ፣ ለኢትዮ-ኤርትራ ድምበር ኮሚሽን የቀረበ ጥሪ"፣ጦቢያ 9ኛ ዓመት ቁ.7 2000 ዓ.ም

ቢደርሳቸውም "የኤርትራ መሪዎች አይወሩንም፤አሳበዱም" በማለት በእንዝህላልነት ችላ በማለታቸው መሆኑን ከሰይ ተገልጾአል። ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት ባድመ እንዲያዝና አገር እንድትደፈር ያደረጉ የፖለቲካ መሪዎች እነማን እንደሆኑ፣ መንግሥትስ ለዚህ እንዝህልልነታቸው ምንስ እርመጃ እንደወሰደ ሕዝቡ የሚያውቀው ነገር የለም።

መሪዎቹ እንደዚህ ተደጋጋሚ ትንኮሳዎችን ችላ ባይሉና እንዝህላልነት ባይንሰራፉ ኖሮ የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ወዲያውኑ እርምጃ ወስዶ አሰብ ዘልቆ ወደቡንና አካባቢውን ሊቆጣጠር በቻለ ነበር።

ኤርትራ ባድመንና አካባቢውን ወርረ ከያዘች በኋላ ለቅቃ እንድትወጣና ቀደም ሲል በነበረችበት እንድትገኝ በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ መንግሥትና በተለያዩ የዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ብትጠየቅ አሻፈረኝ አለች። እንዲያውም "ጅራፍ እራሱ እየመታ እራሱ ይጮሃል" እንዲሉ ኤርትራ በኢትዮጵያ ተወረርኩ በማለት ለአፍሪቃ አንድነት ድርጅትና ለሌሎችም ስሞታ በማቅረብዋ የጦርነቱ ቀስቃሽ ኢትዮጵያ ትሁን ኤርትራ እንዲመረምር በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ተወክሎ እቦታው ድረስ በመሄድ ያጣራው የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ቡድን የሚከተለውን ሪፖርት ለድርጅቱ አቀረበ። "ከ1998-2000 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ውስጥ በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል በተደረገው ጦርነት ኤርትራ በጠብ አጫሪነት የጀመረችው ሲሆን ኤርትራ ራስዋ የቀሰቀሰችው ጦርነት የአልሞት ባይ ተጋዳይነት መከላከል ነበር ልትል አትችልም[146] ብሉ ነበር።

ከሁለት ዓመት ዝግጅት በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ጥቃት ሰንዝሮ ከባድመና ከአካባቢው የኤርትራን ጦር ከማስወጣቱም በላይ ዓለም አቀፍ የጦርነት ደንብ (Rulesof Engagement) በሚፈቅደው መሠረ ወራሪውን ጦር ከአገሩ አስወጥቶ ጦሩን በክትትል ኤርትራ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ በጥቂት ቀናት ውስጥ ሸንበቆን፣ ባሬንቱን፣ አቆቤትን፣ ጾረን፣ መንደፈራን አዲቋላን መያዙን ለኤርትራ ሕዝብ

[146] African Cmmittee of Diplomats, Cited in Abebe Tekle Haimanot Supra Note 3



ቅርብ የሆነው የቦስተን ዩኒቬርሲቲ ጋዜጠኛ ዳን ኮኔል ዘግቦት ነበር። የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል የኤርትራን ሦስት አራተኛ ግዛት ከያዘ በኋላ ልቅቆ እንዲወጣ ታዘዘ[147]።

ጦሩ ግስጋሴውን ቀጥሎ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ያስቻለው የነበረው ሁኔታ በፖለቲካ መሪዎች ድክመት ወይንም ሆን ብሉ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ለማድረግ በመፈለግ የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሰብ ዘልቆ በቁጥጥሩ ስር ማድረግ አልቻለም።

የኢትዮጵያ ጦር በያዛቸው በኤርትራ ግዛቶች ውስጥ አረግቶ አካባቢዎችን ለቅቆ ለመውጣት አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ቅድመ ሁኔታ ቢያደርገው ኖሮ ኤርትራ ይህንን ቅድመ ሁኔታ ከመቀበልና አሰብን ለኢትዮጵያ ከማስረከብ አማራጭ አይኖራትም ነበር።

የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ከመነሻው ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጀምሮ አራቱ ኃያላን አገራትና ሌሎችም የሚደግፉት ነገር ስለነበር በዚህ እርምጃዋ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ነቀፌታ አይደርስባትም ነበር።

በአንዳንድ ጉዳዩን በተከታተሉ ሰዎች ግምት የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሥመራ ዘልቆ የኤርትራን ዋና ከተማ ሲይዝ ይችል እንደነበረ ይናገራሉ። ኤርትራ የዓለም ሕብረተሰብ እውቅና የሰጣት ሉዐላዊ አገር እንደመሆንዋ መጠን የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሥመራን ቢይዝ ኖሮ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤትና ዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ በኢትዮጵያ ላይ ውግዘት ከመሰንዘሩም በላይ ሌላም አስገዳጅ እርምጃ ሊወስድ ይችል ነበር። የጦሩ ወደ አሥመራ ግስጋሴ በአሜሪካኖች ማስጠንቀቂያና ዛቻ ምክንያት እንደቆመም አንዳንድ ውስጥ አዋቂዎች ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሥመራን ሲይዝ ከቻለ ፋቱን ወደ ምሥራቅ አዙሮ አሰብን ነፃ ማውጣት አያዳግተውም ነበር ማለት ነው። ይህንን ቢያደርግ ኖሮ መከላከያ ኃይሉ በአገሩ ላይ ወደር የሌለው ውለታ ጥሎ ነበር። ይህንን ማስፈጸም ይቻል አይቻል እንደነበረ የአገሩ ህልውናና ደህንነት አምኖ ሰስጣቸው የጦሩ አዛገሮች አንድ ቀን ሃቁን ለኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚነግሩት ተስፋ ይደረጋል።

[147] ሪፖርተር እሁድ ሚያዝያ 2 ቀን 2003

የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል በቡሬ ግንባር ከጠላት በሚፋለምበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ፖርላማ ተገኝተው ለፖርላማ አባላት ስለጦርነቱ መግለጫ በሰጡበት ወቅት የመከላከያ ኃይላችን በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳለና ዘልቆ አሰብን ከመያዝ የሚያግደው ምንም ነገር እንደሌለ የኢትዮጵያ ሕዝብና የፖርላማ አባላትን ባስደመመ፤ በጭብጨባ በታጀበ ንግግራቸው አብስረው ነበር።

ኰሎኔል ተወልደ ገብረ ተንሣይም ስለምሥራቁ ግንባር ሲጽፉ ይህንኑ የጠቅላይ ሚኒስትር አባባልን አረጋግጠዋል። ኰሎኔሉ "የኤርትራ መንግሥት ሰኔ 4 ቀን 1990 ዓ.ም. በቡሬ ግንባር በከፈተው ድንገተኛ ማጥቃት የአፋር ሕዝብ ከሠራዊታችን ጐን በመሰለፍ ወራሪውን በጀግንነት ሲገጥም የ52ኛው የኤርትራ ኮማንዶ ክፍል ጦር በውጊያው ተሸንፎ መበተን ሲጀምር በየመንገዱ እያደፈጠ አንድ በአንድ ለቅመውታል" ብለዋል[148]።

ኰሎኔል ተወልደ ገብረ ተንሳይ በመቀጠል የካቲት 7ቀን 1991 ዓ.ም ከንጋቱ 12:30 ላይ በቡሬ ግንባር የተጀመረውና ኢትዮጵያ በአየር ጥቃት ያፋፋመችው ውጊያ የኢትዮጵያ ሚግ 21 ተዋጊ ጀቶች ከኢትዮጵያ ደንበር ወደ ውስጥ 51 ኪሎ ሜትር ዘልቆ በመግባት ከአሰብ 20 ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኘው በርስፌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በኤርትራ ጦር ላይ ድል መቀዳጀቱና በቦታው ተከማችቶ የነበረው የጦር መሣርያና ተሽከርካሪዎች ማውደሙን የኤርትራ ተከላካይ ጦር የኢትዮጵያ ጀቶችን ለመጣል ያደረገው ጥረት እንዳልተሳካለት የኢትዮጵያ መንግስት ቃል አቀባይና አጃንስ ፍራንስ ሬድዮ አረጋግጠው እንደ ነበረ ገልጸዋል። ይህም የሚያሳየው የኢትዮጵያ ጦር ቢፈቀድለት ኖሮ አሰብን ለመያዝ የሚያግደው ምንም ነገር እንዳልነበር ነው። በዚህ አይነት የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሰብ ደርሶ ተመለሰ ማለት ያቻላል።

መከላከያ ኃይላችን ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳረጋገጡት ይህንን ያህል እየቀናው አቅሙም እያለው የኢትዮጵያ ሕጋዊ መብት ወይንም በተባበሩት መንግሥታ አባባል የኢትዮጵያ "ሕጋዊና

[148] ተወልደ ገብረ ትንሳይ (ኰሎኔል) ባድመ እንደ ምክንያት፤ የኛዓግኝው መፃፎ (የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት እውነተኛ ታሪክ) አዲስ አበባ (2008) ገፅ 312



አስፈላጊ" የሆነውን የባህር በር ከጠላት እጅ ፈልቅቆ ነፃ ሳያወጣ የቀረበትና ይህንን የኢትዮጵያ የባህር በር መብት የሰቀቀበት ምክንያት ሕዝቡ ከፖለቲካ መሪዎች መልስ ይፈልጋል።

## 7.11. "ኢትዮጵያ ሽንፈትን ከድል መንጋጋ አወጣች" (ፕሮፌሰር ክላፋም)

እ.አ.አ በ1991 ሻቢያ አሥመራን ሕወሓት/ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በኋላ ኤርትራውያን በኢትዮጵያውያን ጉዳይ ፈላጭ ቆራጭ፤አዛዥና አናዛዥ ሆነው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ኢትዮጵያውያን በገዛ አገራቸው ባዕዳን ሆነው የባንክ ብድርም ሆነ የሥራ ዕድል ለማግኘት ኤርትራውያን ከኢትዮጵያውያን ቅድሚያ የሚያገኙበት ሁኔታ ነበር። ሕወሓትን ያማለለው የኤርትራ ፍቅር በተለያዩ ምክንያቶች ሲያረጅ የአፍሪቃ የዲፕሎማቶች ኮሚቴ እንደዘገበው በኤርትራ ቀስቃሽነት ጦር ተማዛው ጦርነቱ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ቢደመደምም ከጦርነቱ ተጠቃሚ ኤርትራ ሆነች። የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ መምህር ፕሮፌሰር ክሪስቶፎር ክላፋም ስለድንበር ኮሚሽኑ የተዛባ ውሳኔ ሲጽፉ "ውሳኔው ኢትዮጵያ የተጐናጸፈችውን ድል ዋጋ አሳጥቶት ኢትዮጵያ ሽንፈትን ከድል መንጋጋ ፈልቅቃ እንድታወጣ ተገደደች"[149] (Ethiopia pulled defeat from the jaws of victory) በማለት በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን ክስረት ገልጸዋል። ከእነዚህ ክስረቶች ዋና ዋናዎቹ አንዳንድ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶች በኤርትራ እጅ መውደቅና የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ብቻም አይደለም።

ኤርትራ ግን ጦርነት በመቀስቀሰዋ የአሰብ የባህር በር በሕግ ጸደቀላት፤ ጾረና አና ሌሎችንም የኢትዮጵያ ግዛቶች ወደ ኤርትራ ታጠፉ። ሁለቱም አገራት በጦርነቱ ጉዳት ደርሶብኛል ብለው

[149] Christopher Clapham, Professor, "Notes on the Ethio-Eritrea Boundary Demarcation," East Africa Forum, http://www.cfeestees.org/code/claph.htm. Visited on Feb. 2, 2010

ለአልጀርስ የካሳ ኮሚሽን ያቀረቡት ጥያቄ የሁለቱም ጉዳት ተሳልቶ ኢትዮጵያ ለደረሰባት ጥፋት አሥር ሚሊዮን ዶላር ብለሚ ኤርትራ እንድትከፍላት ኮሚሽኑ ወሰነ። ኤርትራ አሥር ሚልዮን ዶላር ብልጫ ለኢትዮጵያ እንድትከፍል ቢወሰንባትም ገንዘቡ እንደማትከፍልና ለመክፈልም አቅሙም እንደሌላት በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። የካሣ ኮሚሽኑም ለሁለቱም ካሣ ሲወስን አገራቱ ሊከፍሉ እንደማይችሉ በመረዳት ነበር በጣም ዝቅተኛ ካሣ የቆረጠው። ኤርትራና ኢትዮጵያ በሰውና በንብረት ላይ ላደረሱት ካሣ ለእያንዳንዳቸው እንዲከፍሉ ታዝዞ የኢትዮጵያ ድርሻ በ10 ሚሊዮን ቢበልጥም የካሣ ኮሚሽኑ ኤርትራ ጦርነት በመቀስቀስዋ ለኢትዮጵያ የቅጣት ካሣ (Punitive damage) እንድትከፍል አልተቆረጠላትም። ኢትዮጵያ በካሣ ኮሚሽኑ ክርክር ባዶዋን ወጣች ማለት ይቻላል ፤ ምክንያቱም ኤርትራ የአይደር ትምህርት ቤትና ከጦርነት ውጭ መሆን የሚገባቸውን አካባቢዎች በቦምብ ስትደበድብ ለዚህ ሁሉ የተፈረደበት የጦር ካሣ አሥር ሚሊዮን ዶላር ብቻ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ካሣ በአሜሪካና አውሮፖ ፍርድ ቤቶች ለስድብ ለሚያህል ትንሽ ነገር ይቆርጣሉ። በአንድ ወቅት በአሜሪካ ውስጥ አንዲት ሴትዮ አንድ ሬስቶራንት ገብታ ቡና አዝዛ ትኩሱ ቡና ጭኗ ላይ ስለፈሰሰ ክስ አቅርባ ሬስቶራንቱ አሥር ሚልዮን ዶላር ካሣ እንዲከፍላት ፍርድ ቤቱ ቆረጠላት።

ምናልባት ወራሪዋ ኤርትራ ወረራ በመክፈትዋና በሸንፈትዋ የከፈለችው ዋጋ ቢኖር በአልጀርስ ስምምነት መሠረት ኢትዮጵያን የሚያዋስነው 25 ኪሎ ሜትር የኤርትራ ግዛት የሰላም ቀጣና ሆኖ የተባበሩት መንግሥት የሰላም አስከባሪ ኃይሎች እንዲሰፍሩበትና እንዲቆጣጠሩት መደረጉ ነበር። ያም ቢሆን የሰላም ቀጣናው ኤርትራ በኃይል መልሳ በእጇ አስገባችው።

ኤርትራ ጦርነት ጭራ ስትሸነፍ የኤርትራ መንግሥት መቀጣትና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት መረጋገጥ ነበረበት። ክጠላት ሲከላከሉ ለወደቁት በአሥር ሺዎች ለሚቈጠሩ ውድ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉት ዜጐች፣ ለጠፋው የግልና የሕዝብ ንብረት ኤርትራ መክፈል ነበረባት። ኤርትራ ግን ለእነዚህ ጥፋቶችዋ ቤሳ ቢስትኒ ሳትከፍል ይልቁንም በከፈተችው ወረራ ተጠቃሚ ሆ



# ምዕራፍ 8

## 8. የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ኢትዮጵያ መሰረዝ ይገባታል

### 8.1 የተኩስ አቁም ስምምነት መጣስ

ስልጀርስ ስምምነት ውስጥ ከተካተቱት ከዋና ዋናዎቹ አንቀጾች አንዱ ስለተኩስ አቁም የሚደነግገው ነው። የዚህ አንቀጽ መጣስ ከሌሎች ጥሰቶች ሁሉ የከፋ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የተኩስ አቁም ጥሰት የስምምነቱ ዋነኛውና አንኳር ዓላማ ስለሚጥስ ነው። ተኩስ ካልቆመ ስምምነቱ ምንም ዋጋ አይኖረውም ማለት ነው።

የተኩስ አቁም ስምምነት ከተደረሰና የአልጀርስ ስምምነት ከተፈረመ በኂላ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታ የኤርትራ ጦር በኢትዮጵያ ጦር ላይ ትንኰሳ ያካሄድ እንደነበር ኢሕአዴግ በተደጋሚ ከስሶ ነበር።

የኤርትራ ጦር በእውነትም ኢሕአዴግ እንደሚለው በተለያዩ ጊዜያት በኢትዮጵያ ጦር ላይ ትንኮሳ ሰንዝሮ ከሆነ ይህም ድርጊት የስምምነቱ ዋናውና አንኳር የሆነውን ተዋዋዮቹ የገቡትን ግዴታ ስለሚጥስ ኢሕአዴግ ስምምነቱን መሻር ይገባው ነበር።

### 8.2. ምሰሶ ወይንም ችካል በወሰኑ ላይ ስለመትከል

የድምበር ኮሚሽኑ የጦርነቱ መንስኤ (Casus Belli) የሆነችውና ከሻቢያ እጅ ለማስለቀቅ እልፍ አእላፍ ኢትዮጵያውያን የተሰዉለት ባድመ ለኤርትራ በመስጠቱ በኢሕአዴግ ሰፈር ከፍተኛ መደናገጥ ተፈጥሮ እንደነበር የሚታወስ ነው። ውሳኔው

የመጨረሻ ይግባኝ የሌለበት መሆኑን እያወቀ ኢሕአዴግ የኮሚሽኑ ውሳኔውን አስመልክቶ ማጣሪያ ጠየቀ።

የማጣርያው ጥያቄው ጉዳዩ እንደገና ይታይልኝ ማለት ስለሆነ ኮሚሽኑ ከእንግዲህ ወሰን አካልሎ ችካል ከመትከል በስተቀር የቀረው ነገር እንደሌለ ገልፆ በኢትዮጵያ ቀርቦ የነበረውን አንድ ጊዜ ይብራራልኝ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደገና በሦስተኛ ወገን ይታይልኝ ብሎ ለተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ም/ቤት ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሆነ።

በሁለቱ ባላጋራዎችና ስምምነቱን በታዘቡ አካላት መሃከል ብዙ ውይይቶች ከተደረጉ በኋላ ኢሕአዴግ ውሳኔውን "በመርሆ" ደረጃ መቀበሉን ገልጾ ድንበር ማካለሉ (Delimitation) ቢጠናቀቅም ምሰሶ ከመቆሙ ወይንም ችካል (Demarcation) ከመተከሉ በፊት የሰዎች አሰፋፈርና የመሬት አቀማመጥ ከግምት ውስጥ አግብቶ "ሰጥቶ በመቀበል" መካለል አለበት ሲል ተከራከረ። ሻቢያ ደግሞ የኮሚሽኑ ውሳኔ የመጨረሻ እንደመሆኑ መጠን ምንም ዓይነት ማስተካከል ሳይደረግ እንደውሳኔው ቃል መፈፀም አለበት በማለት በወሰኖቹ ላይ ችካል እንዲተከል አጥብቆ ጠየቀ። ኮሚሽኑ ሁለቱም መንግሥታት ሊስማሙ እንደሆነ በሚል በቂ ጊዜ ከሰጠ በኋላ ሁለቱም በአቋማቸው ጸኑ።

ኮሚሽኑ ዘመናዊ የአካላል ስልት ተጠቅሜ የድምበር መስመሩ የሚያርፍበት መሬቱ ምን እንደሚመስል ከሰማይ በአይሮፕላን በተነሱ ፎቶግረፎች አይቼ ችካል የሚተከልባቸው ነጥቦችን ለይቼ የማስመሰል ማካለል (Virtual Demarcation) አድርጌ ሥራዬንም አጠናቅቄአለሁ ሲል እ.አ.አ ሕዳር 30ቀን 2007 አስታወቀ። ኤርትራ ይህንን ማካለል በደስታ ስትቀበልው ኢትዮጵያ በጽኑ ተቃወመችው። ኢትዮጵያ ይህንን የማካለል ዘዴ "የሕግ ልብ ወለድ" (Legal Fiction) ነው በማለት እንደማትቀበለው አስታወቀች። ለዚህም የኢትዮጵያ እምቢታ ኤርትራውያን አሜሪካንን ተጠያቂ አድርገዋል። በኤርትረውያን እይታ ኢትዮጵያ ለመካለል ፈቃደኛ ያልሆነችውና የኤርትራ ሉዐላዊ ግዛት የያዘችው የአሜሪካ የገንዘብና የዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ተማምና መሆኑን ኤርትራውያን ሲገልጹ ለዚህም ተወቃሽ ያደረጉዋቸው በቡሽ



አስተደደር ጊዜ የአፍሪቃ ክፍል ረዳት ሚኒስትር የነበሩትን ወይዘሮ ጀንዳይ ፍሬዘርን (Jendayi Fraser) ነው።

ኤርትራ በታላቅ ደስታና ጉጉት የተቀበለችው "የማስመሰል ማካለሉ" ባድመንና ሌሎችም አካባቢዎች ወደ ኤርትራ በማጠቃና ኢትዮጵያን ወደብ አልባ አድርጎ ስለሚያስቀር ነበር። ይህንን መሠረት በማድረግ የኤርትራው ፕሬዘዳንት አቶ ኢሣያስ አፈወርቂ በተለያዩ ጊዜያት በአፍሪቃ ከተደረጉ የድንበር መካለሎች ሁሉ የኤርትራና የኢትዮጵያ ያህል የተዋጣለት አካለል የለም ሲሉ ተናግረዋል። በመቀጠልም በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የድንበር መካለል ችግር የለም፤ ተካልሎ ተጠናቋአልና ብለዋል። በአቶ ኢሳያስ አባባል አሁን የቀረው ኤርትራ በፍርድ የተሰጠት ሉዐላዊ ግዛቶቿዋን በኢትዮጵያ መያዛቸው ነው። ኤርትራ ይህንን ለማስፈጸም ደፋ ቀና የምትል ሲሆን እስከ ዛሬ ሰሚ አግኝታ ኢትዮጵያ በኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት ባድመንና ሌሎችም ለኤርትራ የተወሰኑ ግዛቶች እንድታስረክብ የተደረገባት ግፊት የለም። ኤርትራ በአቶ ኢሣያስ አባባል ኢትዮጵያ በድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት ባድመንና ሌሎችም ለኤርትራ ግዛቶች እንድታስረክብ ያልተገደደችው አሜሪካን ከሳሳ ስለሆነቻት ነው በማለት አሜሪካን እጅግ አምርረው በመውቀሳቸ በዚህም ምክንያት አሜሪካና ኤርትራ በጣም የተበላሸ ግንኙነት አላቸው። በተጨማሪም የአሜሪካና የኤርትራ ግንኙነት የተበላሸው አሜሪካ ኤርትራ የሱማሌ አሸባሪዎችን ትረደለች ከሚልም ጭምር ነው።

የድምበር ኮሚሽኑ የተሰጠው ኃላፊነት ድንበሩን ማካለልና (delimit) ማካለሉም እንደተጠናቀቀ ምሰሶ ማቆም ወይንም ችካል መትከል (demarcate) ነበር። ኮሚሽኑ ያደረገው ግን በኢትጵያና በኤርትራ ካርታ ላይ ከላይ እንዳተገለጸው አንዳንድ ምሰሶ የሚተከልባቸው ነጥቦችን በማስቀመጥ በማስመሰል አካልዬአለሁ፤ ሥራዬንም፤ አጠናቅቄአለሁ በማለት ፋይሉን ዘግቶ ተነሳ።

የድምበር ኮሚሽኑ በአልጄርስ ስምምነት አንቀጽ 4 መሠረት ለኮሚሽኑ የተሰጠው ሥልጣን የሁለቱ አገራት ድንበር ማካለልና ከዚያም በኋላ ምሰሶ በመሬት ላይ ማቆም እንጂ ማስመሰል (Virtual Demarcation) ብሎ ነገር ለኮሚሽኑ አልተሰጠም።

አሁን ኮሚሽኑ ያደረገው የኮሚሽኑ አባላት ወይንም ወኪሎቻቸው መሬቱን ሳይረግጡ በስምምነቱ ያልተጠቀሰው በካርታው ላይ ነጥቦችን ማመላከት ምሰሶን መትከል አይተካም።

ኮሚሽኑ በመሬት ላይ ምሰሶ ማቆም እንጂ በወረቀት ላይ ማመልከት ስምምነቱ ከሰጠው ኃላፊነት ውጭ ከመሆኑም በላይ በማስመሰል መካለል (Virtual damarcation) ምሰሶ በሚቆምበት ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ማረም አይቻልም። በሁለት አገሮች መሃከል ወሰን ተካላሉ ምሰሶዎች በሚተከሉበት ጊዜ አንዳንድ ያልተጠበቁ የመሬት ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ለምሳሌ ምሰሶ የሚቆምበት ሥፍራ እልም ያለ ገደል ሆኖ ምሰሶውን መትከል በፍፁም የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ምሰሶውን ትንሽ ፈቀቅ አድርጐ መትከል የተለመደና በብዙ አገሮች የሚሠራበት ነው። ይህም ማድረግ የሚቻለው በቦታው ተገኝቶ እርምት በማድረግ ሲሆን በወረቀት ላይ የሚደረገው ምልክት ይህ መታረም ያለበትን ጉራማይሌ ሁኔታ ሊያሳይ አይችልም።

የድምበር ኮሚሽኑ በዚህ ሕጉ በማያውቀውና ስምምነቱ ውስጥ ባልተገለፀ የማስመሰል ማካለል አድርጌአለሁ ማለቱ ከተሰጠው ኃላፊነት ውጭ ስለሆነ ስምምነቱን መጣስ ነው። ስለዚህ ስምምነቱ በሚያዝዘው መሠረት በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የድምበር ምሰሶ አልተተከለም ማለት ሲሆን ኮሚሽኑም ምሰሶዎችን ከመትከሉ በፊት ሥራውን በማቆም ስምምነቱን ስለጣሰ ኢሕአዴግም ስምምነቱንም ሆነ የድምበር ኮሚሽኑን ውሳኔ መሻርሙሉ መብቱ ነው።

ከዚህ በላይ የተዘረዘረው "የማስመሰል" ምሰሶ ተክዬአለሁ በማለት የድምበር ኮሚሽኑ በአልጀርስ ስምምነት የተሰጠውን ኃላፊነት መጣሱና ስምምነቱን ማፍረሱ እንዳለ ሆኖ ኤርትራም ስምምነቱን ከአራት ጊዜ ባላነሰ ስትጥስ ኢሕአዴግ ለድምበር ኮሚሽኑም ይሁን ስምምነቱን ለማስፈጸም ለተመደቡ አካላት አንድም ጊዜ ይፋዊ ተቃውሞ ሲያሰማ አልተደመጠም።



## 8.3. አንዳንድ የሰላም አስከባሪ ኃይል አባላት ከኤርትራ መባረር

የሁለቱን አገራት ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት ከተቋቋመው የሰላም አስከባሪ ኃይል (United Nations Mission in Ethiopia and Eritrea) (UNMEE) ውስጥ ኤርትራ አንዳንድ አሜሪካኖችን፣ አውሮፓውያንን ካናዳውያንና ሩሲያውያንን ከአገር አባረረች[150]።

ሁለቱ አገራት ተካልለው ወሰኖቻቸውን ለመለየት ምሰሶ እስኪያቆሙ ድረስ የሰላም አስከባሪው ኃይል በሰላሙ ቀጣና እንዲቆይ ስምምነት ተደርሶ ነበር። ሆኖም ምሰሶዎች ተተክለው የድምበር መካለሉ ሥራ ከመጠናቀቁ በፊት ኤርትራ አንዳንድ የሰላም አስከባሪ አባላትን ማባረሯ ስምምነቱን መጣስ ነው። ስለሆነም አሁንም ስምምነቱን ኤርትራ መጣስዋን ኢሕአዴግ እያወቀ ስምምነቱና ውሳኔውን ለመሰረዝ በቂ ምክንያት እያለ በዝምታ ማለፍን መረጠ።

ኤርትራ እነዚህን ጥሰቶች በመፈጸምዋ ስምምነቱ ተሰረዘ ማለት አይደለም። ኤርትራ ስምምነቱን ስትጥስ ኢትዮጵያ ስምምነቱን የመሰረዝ መብት ይሰጣታል እንጂ ስምምነቱ ተሰረዘ ማለት አይደለም። ኢሕአዴግ የድምበር ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔና ስምምነቱ በግልጽና በይፋ ሽሮ መሻሩንም ለድምበር ኮሚሽኑና ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አስታውቆ ውሉን የሻረበት ሰነድ በተባበሩት መንግሥታት አርካይቭ ሲቀመጥ ብቻ ስምምነቱ እንደተሻረ ሊቆጠር ይችል ይሆናል። ኢሕአዴግ ስምምነቱ በሻቢያ መጣሱ በተለያዩ ጊዜያት በሚዲያ ቢገልጽም ራሱ ኢሕአዴግ

[150] Afop News, 7 December 2000.

ስምምነቱን ስለመሰረዙም ሆነ የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ስለመሻሩ ያለው ነገር የለም። እንዲህ ዓይነት ክርክር በሚነሳበት ጊዜ "ዝምታ" በሕግ ፊት የሌላውን አቋም እንደመቀበል ይቆጠራል። (Silence is acceptance)። ስለሆነም ኤርትራ የአልጀርስ ስምምነቱም ሆነ ውሳኔውን ምን ጊዜም ልታነሳው ትችላለች።

በግልግል ዳኝነት የተወሰኑ እንዲያውም ከግልግል ዳኝነት በላይ ክብርና ክብደት ያላቸው በተባበሩት መንግሥታት ዋና የፍትሕ አካል በሆነው በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት (Internaitonal Court of Justice) የተወሰኑ ጉዳዮች እንኳን መሻር ወይንም ውሳኔውን አልቀበልም ማለት የተለመደ ነው።መንግሥታቱ በመረጡአቸው ዳኞች ፊት ቀርበው ከተከራከሩ በኋላ ወይንም ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቀርበው ከተረቱ በኋላ የግልግል ዳኞች ወይንም የፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሠረታዊ ጥቅሞቻቸውን የሚጻረሩ ከሆኑ ውሳኔዎቹን አንቀበልም ያሉባቸው አያሌ ጊዜአት አሉ።

መንግሥታት እንደዚሁ መሠረታዊ ጥቅሞቻቸውን የሚጐዳ መስሎ በታያቸው ጉዳይ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በተከሰሱ ጊዜ ክሱን ተቀብሎ ፍርድ ቤት መቅረብ እንኳን ፈቃደኛ ያልሆኑባቸው ጊዜያትም አሉ። አንድ ያውል ግዴታን ወይንም የፍርድ ቤት ውሳኔ አክብሮ መፈጸም አገሪቱን የሚያጠፋ ከሆነ የውል ግዴታን ከመፈጸም በፊት ሕልውናን በማስቀደም ውሉን መሰረዝ ይችላል የሚለው የቆየ የሕግ መርሆ አለ ።[151]

ላለመግባባቱ መንስኤ የሆነው ጉዳይ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት እይታ ለዓለም ሰላምና ጸጥታ አስጊ መስሎ ካልታየ የተባበሩት መንግሥታት የፍርድ ቤትንም ወይንም የግልግል ዳኞች ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ እንዲፈጽሙ ማስገደድ አይቻልም። ስለሆነም መንግሥታት የግልግል ዳኝነት ወይንም የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መጥሪያም ሆነ ውሳኔ አንቀበልም ያሉባቸውና በዚህም ምክንያት ምንም ችግር ያልገጠማቸው አገራት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

[151] See Jefferson Opinion on the French Treátires (Qpr.28,1793) in Merril D.Peterson,Ed, The Politcal Writings of Thomas Jefferson,113-114 (Thomas Jefferson Memorial Foundation:1993) p.113-114



እ.አ.አ በ1974 ዓ.ም ፈረንሳይ በፖሲፊክ ውቅያኖስ በኒውዚለንድና በአውስትራልያ አካባቢ የኑክሌር ቦንብ ሙከራ ልታደርግ በወሰነች ጊዜ እነዚህ ሁለቱ አገራት ሙከራው እንዳይደረግ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ክስ መሠረቱ። ፍርድ ቤቱ የሁለቱንም ክርክር ከሰማ በኋላ ፈረንሳይ የኑክሌር ሙከራውን እንድታቆም ቢበይንም ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታ ውሳኔውንም እንደማትቀበል ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አስታወቀች። የኑክሌር ፍንዳታ ሙከራም አደረገች[152]።

እንዲሁም የደቡብ አሜሪካዊት አገር ኒካራግዋ አሜሪካ ወታደራዊና ሌላም ሌላም ጥቃት አድርሳብኛለች በማለት በ1984 ዓ.ም በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ክስ አቅርባ ነበር። ፍርድ ቤቱም አሜሪካ የኒካራግዋን የተለያዩ መብቶች መጣሰዋ ጠቋሚ ማስረጃዎች ቢኖሩም አሜሪካ እንዲያውም የፍርድ ቤቱን ሥልጣን አልቀበልም ብላ ለክሱ ፍሬ ነገር መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነችም። በሌለችበት የተሰጠውንም ውሳኔ አልቀበልም አለች።

አንድ የጀርመን ዜጋና ወንድሙ አሜሪካ ውስጥ በሠሩት ወንጀል እ.አ.አ. በ1998 ዓ.ም በአሜሪካ ፍርድ ቤት የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ጉዳያቸው ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወስደው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የሞት ቅጣቱ እንዲታገድ ቢያዝም አሜሪካ ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታ ሁለቱም ወንድማማች በሞት ተቀጡ[153]።

ኢትዮጵያ የድምበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ብትሰርዝ ተጨባጭ የሆነ ምንም ዓይነት ጫና ወይንም ቅጣት የሚደርስባት አይመስልም። ዛሬ ሻቢያ በተለይም በአሜሪካና በአውሮፖ እንደ ወንበዴ መንግሥት (rogue state) በተቆጠረችበትና ከዚያም አልፎ

[152] Tekola W.Hagos, Professor, "Aklilu Habtewold: In the Footsteps of a Great International Law Jurist Disqualification of Lauterpacht: Nullification of Algiers Agreement, and Rejection of the Decision of the Border Commission." Phineaus Claire Washington DC October 30, 2003,

[153] Ibid

የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ኤርትራ በሱማልያ ያለውን መንግሥት ለመጣል ለሚሠሩ ቡድኖች ድጋፍ ታደርጋለች፤ከጅቡቲ ጋር ያላት የድምበር ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመጨረስ ፋቃደኛነት አላሳየችም በማለት እ.አ.አ በፌብርዋሪ 25 ቀን 2010 ዓ.ም የጦር መሣርያ እቀባ፤ የአገሪቱን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከአገር ውጭ እንዳይዘዋወሩ እንዲሁም ባለሥልጣናቱ በውጭ ያላቸው ንብርት እንዳያንቀሳቅሱ በተደረገበት ሁኔታ ኢትዮጵያ የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ሽራለችና ማዕቀብ ይጣልባት ብትል ኤርትራ ሰሚ አታገኝም። ለዚህም የብሪታንያ የውጭ ጉዳይና በኮመንዌልዝ የአፍሪቃ ዲሬክተር ሚስተር ጀምስ በሻንን መጥቀስ ይቻላል። ኢትዮጵያ የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ ባትቀበል የብሪታንያ መንግሥት ማዕቀብ የመጣል እቅድ አለው ወይ ተብለው ለተጠየቁት ቀጥሉ ያለውን መልስ ሰጡ። “የድምበር ኮሚሽኑ ያስተላለፈው ውሳኔ ለመቀበል ኢትዮጵያ ሊከብዷትና አሉታዊ ጐኑ ያመዘነ ጠንካራ ስሜት ሊፈጥር ይችላል። የብሪታንያ መንግሥት በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ ማዕቀብ የመጣል አቋም የለውም፤ ምክያቱም ማዕቀብ መጣል ምንም ፋይደ የለውም። ስለዚህ የብሪታንያ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት ከዛሬ ጀምሮ የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ካልተቀበልክ ምንም ዓይነት የገንዘብ እርዳታ አልሰጥህም የሚል አቋም የለውም”[154]። በተለይም ኢሕአዴግ ሽብርተኛነትን በመዋጋት የምዕራባዊያን ምርጥ ወኪል በሆነበት በአሁኑ ሰዓት ውሳኔውን ቢሽር ማንም ደፍሮ የኢኮኖሚ እቀባም ሆነ የኃይል እርምጃ ይወስድበት የሚል የለም። የድምበር ኮሚሽኑ በወሰነው መሠረት ኢትዮጵያ ለኤርትራ እንድታስረክብ የተፈረደባትን ባድመንም ሆነ ሌሎች አካባቢዎችን እንድታስረክብ አምርሮ የጠየቃት እንኳን የለም። ምናልባት ሁኔታው ከፍቶ በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ እቀባ ይደረግባት ቢባል እንኳን ከዚህ ቀደም በአገራት ላይ የተጫኑ ማዕቀቦች ውጤት አልባ ሆነው የተፈለገው ዓላም ማስፈፀም አልቻሉም። ለዚህም ከኤርትራ የተሻለ ምሳሌ አይገኝም። ኤርትራ በሱማልያ ሽብርተኞችን ትረዳለች በሚል በአብዛኛው በኢትዮጵያ ቀስቃሽነት የተጣለባት የኢኮኖሚ እቀባ ያደረሰባት ጉዳት አይታይም። የኤርትራው ፕሬዚዳንት የተጣለው ማዕቀብ

[154] ኒሽን ጥቅምት 28 ቀን 1996 ዓ.ም



በኢኮኖሚአቸው ላይ ምንም ዓይነት ጫናም ሆነ ጉዳት እንዳላደረሰ ብዙ ጊዜ ተናግረዋል።

አቶ መለስ ስምምነቱን ቢሽሩት በኢትዮጵያ ላይ የሚደርሰ ጉዳት እስለመኖሩን በአንድ ወቅት ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪቃ ክፍል እርዳት ሚኒስትር ለወይዘሮ ጀንዳይ ፍሬዘር (Jendayl Fraser) ገልጸውላቸዋል። ወይዘሮዋ አዲስ አበባን ጐብኝተው ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር ተገናኝተው ስለ ሰላም አስከባሪው ኃይል ከኤርትራ መባረር ባደረጉት ውይይት ወይዘሮ ፍሬዘር ኢትዮጵያ የአልጀርስ ስምምነትን ብትሰርዝ ምን ይደርስባታል ብለው አቶ መለስን ጠየቋቸው።አቶ መለስም ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ኢትዮጵያ ውሉን ብትሰርዘው “በመንግሥታቸው ውስጥ ያሉት ተቃዋሚ አክራሪዎችን ያጠናክራል። እነዚህ አክራሪዎች በኤርትራ ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ እንዲወሰድ ይፈልጋሉ፤ኤርትራውያንም ግራ ይጋባሉ”[155] በማለት ጥያቄውን መለሱ። በመልሱ፤ አክራሪዎች ይጠናከራሉ ሲሉ ለአቶ መለስና ለቡድናቸው ሥልጣን ስጋት ይሆናሉ ማለታቸው ግልጽ ነው። በዓለም ሕብረተሰብ ኢትዮጵያ የድምበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ባለማክበርዋ ምናልባት ሊደርስባት የሚችለው ጫና አላነሱም።

## 8.4. የሰላም ቀጣናው በኤርትራ ጦር መወረር

ኤርትራ ስምምነቱን ስትፈርም ጦርዋ የኢትዮጵያ ጦር ከነበረበት ከኤርትራ ወሰን 25 ኪሎ ሜትር እርቆ በኤርትራ ምድር እንዲሰፍርና ላይ ታቹ ስፋቱ 25 ኪሎ ሜትር የሚሆን የሰላም ቀጠና በመሬትዋ ላይ ተመስርቶ የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪ ወታደሮች (United Nations Mission in Ethiopia and Eritrea) እንዲሰፍሩበት ተስማምታ ነበር። ኤርትራ እራስዋ በቀሰቀሰችው ጦርነት በመሸነፍዋ የከፈለችው በጣም ትንሽ ዋጋ ቢኖር ይህ የሰላም ቀጠና በመሬትዋ ላይ መቋቋሙ ነበር።

[155] See .http://danielberhane .wordpress.Com Accessed on 6 june 2011

ይህ መሬት በተባበሩት መንግስታት በተቋቋመው የሰላም አስከባሪ ኃይል ቁጥጥር ሆኖ ኃይሉ እንደፈለገ እንዲንቀሳቀስና የሰላሙን ሁኔታ እንዲቆጣጠር በስምምነቱ ተፈቅዶለት ነበር። ሆኖም ኤርትራ የሰላም አስከባሪውን ኃይል እንቅስቃሴን በመገደብና የተለያዩ ጫናዎችን በማድረግ፤ ለምሳሌ ነዳጅ እንዳይገዙ መከልከልን የመሳሰሉ ድርጊቶች በመፈጸም የሰላም አስከባሪው ኃይል ተግባሩን እንዳያከናውንና አላፊነቱን እንዲይወጣ ብዙ እንቅፋቶች ተጋረጡበት። በመቀጠልም ኤርትራ የሰላም ቀጠናውን ጥሳ ገብታ በጦር ኃይል በመቆጣጠሯ በሁለቱ አገራት ወሰኖች ምሰሶ ቆም እስኪጠናቀቅ በቦታው መቆየት ይገባው የነበረው የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪው ኃይል ሥራውን አቋርጦ እ.አ.አ በጁላይ 2008 ዓ.ም የሰላም ቀጣናውን ዘግቶ እንዲወጣ ተገደደ። አሁንም ኤርትራ የሰላም ቀጣናውን ስትቆጣጠር ስምምነቱን እንዳገና ጥሳዋለች። ይህንን ጥሰት ተከትሉ ኢሕአዴግም ስምምነቱንና ውሳኔውን ሊሽር ቢችልም አሁንም በዝምታ አልፎታል።



ምዕራፍ 9

# 9. የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን አስመልክቶ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሲቪክ ማህበራትና የሕዝባዊ ድርጅቶች አቋምና ያደረጉአቸው ትግሉች

## 9.1 የፓለቲካ ፓርቲዎች

ኢሕአዴግ አሰብ የኤርትራ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋና ለባለቤትዋ ለኢትዮጵያ እንድትመለስ አሁንም ሆነ ወደፊት ዲፕሎማሲያዊ ጥረትም ሆነ ከኤርትራ ጋር ድርድር እንደማያደርግ በተለያዩ ጊዜያት በግልፅና በማያሻማ መልኩ አረጋግጧል። የኢሕአዲግን አቋም እንደፓርቲነቱ ከለይ በዝርዝር ስለተብራራ አሁን እዚህ አንመለስበትም።

በምርጫ 97 የተወዳደሩና ከዚያም በኋላ የተፈጠሩ ፓርቲዎች በፕሮግራሞቻቸው ካሰፈሩአቸው ከዋና ዋና ተግባሮቻቸው አንዱ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመልስ መሥራት መሆኑን አረጋግጠዋል። በምርጫ 97 የአሰብ ወደ ኢትዮጵያ መካለል ፓርቲዎች ከሕዝቡ ድጋፍ ለማግኘት በሰፊው ከተጠቀሙባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ኢሕአዴግ ስለ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ያለው እጅግ የላላ አቋምና አሰብን ለኤርትራ አሳልፎ መስጠቱ ነበር ቢባል የተሳሳተ ግምት አይሆንም። አሁንም ቢሆን ብዙዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ ሲቪክ ማህበራትና፤ሕዝባዊ ድርጅቶች አሰብን የማስመለስ ጉዳይ ሊሸሹት የማይችሉት ነገር ሆኖ በየፕሮግራሞቻቸው ቀርጸው ለዚሁ ግብ እንደሚሠሩ ቃል ገብተዋል።

## 9.2. በ1997 ዓ.ም ብሔራዊ ምርጫ አሸንፎ የነበረው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ (ቅንጅት) በሕዝብ ዘንድ የነበረው ተቀባይነት ሰዎች ለቅንጅት ድል ሞትን እንኳን የተጋፈጡበት ከብዙ ምክንያቶች አንዱ በብሔር ወይንም በዘር ያልተከፋፈለ በአንድነት የተሳሰረ ሙሉ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ያንፀባርቅ ስለነበር ነው፡፡ የዚህም መገለጫው በኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና የኢትዮጵያን ጥቅም በማስጠበቅ ቅንጅት የነበረው ጠንካራ አቋም ነበር፡፡ ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብን ከዳር እስከ ዳር ካንቀሳቀሰባቸው ከዋነኛ ፕሮግራሞቹ አንዱ ሉዐላዊነትን የማስከበር ዓለማ የሆነውን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማካለል የነበረው ቁርጠኝነት ነበር ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡ ቅንጅት ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ለአሰብ ኢትዮጵያዊነት የነበረው ቁርጠኝት ሕዝቡ ጠንቅቆ ከማወቁም በላይ በሕዝቡ እንዲሰርጽ ለማድረግ ችሎ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ በአገሩ ሉዐላዊት የሚነሳ ጥያቄ ያህል የሚቀሰቅሰው ምንም ነገር ያለ መኖሩን ያህል በዚሁ ምክንያት ቅንጅትን ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ አቀፈው፡፡ ከምርጫው ትንሽ ቀደም ብሎ በኢሕአዴግና በቅንጅት ተወካዮች መሃከል በተደረጉት ክርክሮች ለኢሕአዴግ በዝረራ መሸነፍ አንዱ ምክንያት ኢሕአዴግ በሉዐላዊነት ላይ የነበረው የተለሳለሰ አቋም በተለይም አሰብ የኤርትራ ግዛት ነች በማለቱና አሰብንም ለማስመለስ ምንም ጥረት እንደማያደርግ ግልጽ በማድረጉ ነበር፡፡

በምርጫ 97 እና ከዚያም ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ የህዝቡ ጥያቄ ለዲሞክራሲ ለፍትሕና ለእኩልነት ብቻ አልነበረም፡፡ በይበልጥም የኢትዮጵያ ሉዐላዊነት መከበርንም ይጨምር ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ በራፋችን ደርሰው በኢሕአዴግ የተቀለበሱት እነዚህ የዴሞክራሲ እሴቶች ጥያቄ እንደተጠበቁ ሆነው፤ ከእነዚህ ጎን ለጎንና መሳ ለመሳ የቆመው የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በየምርጫ ወረዳዎች ከምርጫ መፈክሮችና ከተለጠፉ ፖስተሮች ውስጥ አሰብን ወደ ኢትጵያ የማስመለስ ጥያቄ ጎልቶ ይታይ ነበር፡፡ ለናሙና ያህል በጉራጌ ዞን በቸሀ ወረዳ በእምድር ከተማ ምርጫው ሁለት ቀን ሲቀረው የሆነውን እንጥቀስ ፡፡ ከሊቅ እስከ ደቂቅ የእምድብር ሕዝብ



የቅንጅት ተወዳዳሪዎችን ለመደገፍ ተነቅሎ ወጥቶ የቅንጅት ተወዳዳሪዎችን ያሳሰብ የነበረው የምግብ ወይንም የውሃ ወይንም የጤና አገልግሎት ጥያቄ ሳይሆን ሕዝቡ እዚያችው በፈጠረው ስንኝ

*የዛሬ ዓመት የዛሬ ዓመት*
*አሰብ የእኛ ናት*

እያለ በሚዘምረው ማሳሰቢያ ነበር፡፡ ሕዝቡ ይህንን ያዜም የነበረው ቅንጅት አሸንፎ ሥልጣን እንደሚይዝ እርግጠኛ ስለነበር፤ ቅንጅት ሲያሸንፍም አሰብን ያስመልሳል ከሚል ፅኑ እምነት ከመነሳት ነበር፡፡ የቅንጅት አመራሮች ይህንን የሕዝብ ስሜት ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር የምረጡኝ ዘመቻ ከመጀመሩ በፊት ባወጡት የቅንጅት የምርጫ ማኒፌስቶ የሚከተለውን አስፍረው ነበር፡፡

*"የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ ሕጋዊና የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብም በሚገባ የሚገነዘበው ቢሆንም የገዢው ፓርቲ በያዘው የተሳሳተ አቋም ለውይይት እንኳን የሚቀርብበት እድል ተዘግቶአል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥያቄ ከሉዓላዊነትና ከብሔራዊ ሕልውና ጋር የተያያዘ ሕጋዊ ጥያቄ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩ በሰላማዊ መንገድና በሁለቱ ሕዝቦች ስምምነት መፍትሔ እንዲያገኝ ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ድጋፍ እንዲሰጥ ጥረት ያደርጋል"*[156]

በማለት ቅንጅት አሰብን ለማስመለስ የወደፊት ትግሉን ቀይሶ ነበር፡፡ በግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫ የሕዝቡ ድምጽ ዋጋ ተሰጥቶት ውሳኔው ተከብሮ ቅንጅት እንደ ሕዝቡ ውሳኔ ሥልጣን ቢረከብ ኖሮ ከቀዳሚ የቅንጅት አጀንዳዎቹ አንዱ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት የሆነችውን አሰብን ወደ ባለቤቱ ወደ ኢትዮጵያ ማስመለስና የቀይ ባህር አፋሮች አንድነት በማረጋገጥ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብታቸውን ማስከበር ነበር፡፡

አሰብን ለማስመለስ የቅንጅት እንቅስቃሴ የሚጀምረው ከዲፕሎማሲ አቅጣጫ ይሆን ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ የባህር በር እንዳትኖራት በተለያዩ መድረኮች ይደግፉ የነበሩ

[156] <u>የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የምርጫ ማኒፌስቶ</u>፤ አዲስ አበባ 1997 ዓ.ም

አሜሪካ፣ ፈረንሳይ ታላቋ ብሪታንያና ራሽያ አሁንም በቃላቸው ተገኝተው የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እንዲደግፉ መጠነ ሰፊ ዘመቻ ይከፍት ነበር። እንዲሁም በአፍሪቃ ተመሳሳይ ዘመቻ ተከፍቶ አገራቱ ድጋፋቸውን እንዲሰጡ ይጠየቁ ነበር። ከዚያም መግባቢያ ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ አማራጮች* ለኤርትራ አቅርቦ መደራደር በተቻለ ነበር።

ቅንጅት የዲፕሎማሲ ጥረቶችን አሟጦ ለኤርትራ የሚቀርቡ አማራጭ ሐሳቦች በኤርትራ ተቀባይነት ካላገኙ የመጨረሻው ሰላማዊ መንገድ ጉዳዩ ወደ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) በመውሰድ ከፍርድ ቤቱ ፍትሕ መጠየቅ ሌላው አማራጭ በሆነ ነበር።

ቅንጅት በምርጫ ሚኒፌስቶውና በፕሮግራሙ የተገለጹት ለኢትዮጵያ ብሩህ ቀን ያፈነጥቃሉ የተባሉት ተግባራት በሥራ ላይ ሳያውል ሁሉም እንደሚያውቀው በኢሕአዴግ፤ በተለያዩ አካላትና ግለሰቦች በተፈጸመበት ደባ ምክንያት እጅግ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ፈረሰ። ከቅንጅት መፍረስ ጋርም አሰብን ወደ ኢትዮጵያ የማስመለስ ዕድል ለጊዜው ያከተመ ቢመስልም ወቅቱን ጠብቆ አንድ ቀን መነሳቱ ግን አይቀርም። ምክንያቱም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ቁጥሩ ከመቶ ሚልዮን በላይ የሚሆነው ሕዝብ በእግር መንገድ እርቀት የሚገኘው ብቸኛ የባህር በሩ ተዘግቶበት ፀጥ ብሎ እንዲኖር መጠበቅ ከፍትሕና ከመልካም ጉርብትና ጋር የማይጣጣምና በተቃርኖ የሚቆም ሁኔታ ነው የሚሆነው። ከፍትሕ በተቃርኖ የቆመ ሁኔታ ሁሉ ጊዜ ይወስድ እንደሆነ ነው እንጂ በፍትሕ መሸነፉ የማይቀር ነው።

## 9.3. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አንድነት መድረክ

መድረክ እራሱና የመድረክ አባል ፓርቲዎች በኢትዮጵያ የባህር በር መብት ላይ የፀና አቋም ያላቸው ሲሆን ሁሉም በግልፅና በማያሻማ መልኩ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ እንደሚሠሩ በየፕሮግራሞቻቸው ውስጥ ቀርፀውት ይገኛል።

---

* አንዳንድ አማራጮች በጽሁፉ መጨረሻ ተዘርዝረው ተተንትነዋል



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) በመሰስተኛ ፕሮግራሙ የሚከተለውን አስፍሮአል።

*"ኤርትራውያን [ከወደብ] ጋር በተያያዘ ሊኖራቸው የሚችለውን ስጋት ለመቅረፍ እና ሁለቱም ወገኖች ተጠቃሚ ሆነው የሚወጡበትን የመፍትሔ አማራጮችን (መድረክ) ያፈላልጋል። ኢሕአዴግ መንግስት ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ላይ ያላት ከታሪክ ከዓለም አቀፍ ሕግጋት እና ከፍትሐዊነት አንፃር የባለቤትነት መብትዋን ሳያስከብር ቀርቷል። ይህም በመሆኑ ሃገራችን ወደብ አልባ በመሆንዋ ምክንያት በአስከፊ ኢኮኖሚያዊና የፀጥታ ችግሮች ውስጥ እንድትገባ አድርጓል። ስለዚህ የአሰብ ወደብ ለኢትዮጵያ የምትገባ የባህር በር መሆንዋን በመገንዘብ በዚሁ ጉዳይ ከኤርትራ ጋር የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ጠንካራ ዘላቂ ስምምነት ላይ መድረስ እንደሚገባ መድረኩ በፅኑ ያምናል። ለዚህ ስኬት ኢትዮጵያውያን በጽናት እንዲቆሙ ያለመታከት ይሠራል"*[157] በማለት ዕቅዱን ገልጾአል።

በአንድ ወቅት የአሁኑ የመድረኩ ሊቀመንበርና የአረና ፓርቲ መሪ አቶ ገብሩ አሥራት "አሰብ የኢትዮጵያ ንብረት እንደሆነ ሕጋዊም ታሪካዊም መረጃ አ ለን። .....በህጋዊና በፖለቲካዊ መንገድ ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ማድረግ እንፈልጋለን። መንግስቱ (ኢሕአዴግ) የአሰብን ጉዳይ ማንሳት ሰላምን ያናጋል፤ ጦርነት ይቀሰቅሳል ፤ኢትዮጵያን ከጎረቤቶችዋ ጋር ማበጣበጥ ነው ብሎ ያምናል። መንግስት የሚከራከረው ለእኛ ነው. ወይስ ለኤርትራ የሚለው ጉዳይ መነሳት ያለበት ይመስለኛል" በማለት መድረክ ስለ ባህር በር ያለውን አመለካከት አብራርተዋል። የመድረኩ አቋም ጠንካራና የማያወላውል መሆኑ ግልፅ ሲሆን ለባህር በር ያለ መታከት እንደሚሠራ ቃል ገብቶአል። ሆኖም ይህ መሰስተኛ ፕሮግራም ከተዘጋጀ ወዲህ መድረክ አሰብን አስመልክቶ ምንም ያደረገው ነገር የለም። ምናልባት በአገራችን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ሰላማዊ ሰልፍ የመሳሰሉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችን የማይፈቅድ ቢሆንም ከሰላማዊ ሰልፍ መልስ፣ ፅሁፎችን አውጥቶ ሕዝቡን ስለአሰብ ግንዛቤ ማስጨበጥ የባህር በር ጥያቄ ከሕዝቡ ሕሊና እንዳይወጣ የመሳሰሉ ነገሮችን በመሥራት የመሪነት ግዴታውን መወጣት ይጠበቅበታል።

---

[157] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ መሰስተኛ ፕሮግራም አዲስ አበባ 2001ዓ.ም

## 9.4. የዓረና ትግራይ ለደሞክራሲና ሉዐላዊነት ፓርቲ (ዓረና)

የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋትና ወደብ አልባ መሆን ከሚቆጠቁጣቸው ኢትዮጵያውያን ውስጥ የዓረና ትግራይ ለዲምክራሲና ሉዐላዊነት (ዓረና) ፓርቲ መሪ አቶ ገብሩ አሥራትና አባላቱ ናቸው። በሚድያ አማካይነትም ይሁን በሌላ አጋጣሚ ወደ ሕዝብ በሚቀርቡበት ጊዜ ሁሉ የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ብሎም አሰብን ወደ ኢትዮጵያ የማጠቃን ጉዳይ ሳያነሱ ያለፉባቸው ጊዜያት የሉም ማለት ይቻላል። የዓረና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊም አቶ አስራት አብርሃም በጻፉት <u>ከአገር በስተጀርባ 2003 ዓ.ም</u> በተሰኘው መጽሐፋቸው ለኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ትኩረት በመስጠት የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት የሚያስከትለውን ጉዳት በብዙ ቦታዎች ይተነትናሉ[158]። አቶ ገብሩ አሥራት ከሕወሓት መሪዎች አንዱ በነበሩበት ጊዜ ከተደረጉ ጥፋቶች ሁሉ የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆን በቀዳሚነት ያስቀምጡታል። ከዚህ ቀደምም ለዚህ ጥፋት ከአንዴም ሁለቴ በድፍረት ወጥተው፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቃቸው ያስመሰግናቸዋል።

ዓረና ስለኢትዮጵያ የባህር በር መብት በፕሮግራሙ ሰፊ ቦታ ሰጥቶ አስተናግዶታል። በዚህ መሠረት ዓረና "ከዓለም አቀፍ ሕግጋትና ከታሪክ አንጻር [ኢትዮጵያ] ራስዋ ባለቤት ሆና የምታስተዳድረው የባህር በር እና መተላለፊያ (ኮሪደር) የማግኘት መብት እንዳላት ዓረና ያምናል[159]። የባህር በር ጠቃሚነቱ "ለኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን የአገር ደህንነትና ሕልውና ጉዳይ መሆኑንም ይገነዘባል"[160] ዓረና የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ለማስከበር የሚሠራ ሲሆን "በደብልዮ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ

[158] አሥራት አብርሃም ዝኒ ከማሁ 16
[159] የዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ሉዐላዊነት [illegible] ነሐሴ 22 ቀን 2002 ዓ.ም
[160] ዝኒ ከማሁ



በዲፕሎማሲያዊና ሰላማዊ ትግል [አሰብን ለማስመለስ] በጽናት እንዲቆም ያለ መታከት"[161] እንደሚሠራ ቃል ገብቶአል።

## 9.5. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፖርቲ (ኢዴፖ)

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፖርቲ አሰብ በኤርትራ እጅ ወድቆ የኢትዮጵያ የባህር በር ተዘግቶ አገሪቷ ወደብ አልባ መሆን በአገሪቱ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከሁሉም ፖርቲዎች ቀደም ብሎ የተገነዘበ ሲሆን በተለያዩ ወቅቶች መግለጫዎችን በማውጣት ሰላማዊ ሰልፎች በተደረጉበት ጊዜያት ሁሉ የባህር በር መብትን በተለይም የአሰብን ኢትዮጵያዊነት አጉልቶ በማሳየት የሕዝቡ ግንዛቤ እንዲዳብር በብዙ ደክሞአል። የፖርቲው ሊቀ መንበር አቶ ልደቱ አያሌው በ1983 ዓ.ም. ለሪፖርተር ጋዜጣ እንደገለጹት "ይህን ፍትሐዊ ጥያቄዋን [አሰብ ወደ ኢትዮጵያ መታጠፍ ይገባዋል የሚለውን ማለት ነው] በአግባቡ በጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ሊታገል የሚችል ኃይል ባለመኖሩ እንጂ የኢትዮጵያ የባህር በር የሌላት ዝግ አገር አትሆንም ነበር" በማለት ቁጭታቸውን ገልጸው የዛሬው ትውልድ ትግሉን ይጀምር፤ ቀጣዩ ትውልድ ደግሞ ይጨርሰዋል ሲሉ ተሰፋቸውን ገልጸዋል። ኢዴፖ እንዳጀማመሩ ሳይሆን በአሁን ጊዜ እንደሌሎቹ ፓርቲዎች ሁሉ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማጠፍ ምንም እንቅስቃሴ ሲያደርግ አይታይም። ይህም ፖርቲ በመጀመርያ የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት እንዳሳሰበውና እንዳስጨነቀው ያህል አሁንም በትግሉ አመራር እንዲሰጥ ይጠበቅበታል፡

## 9.6. የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር

አሰብ ወደ ኤርትራ እንዳይካለል ከፍተኛ ጥረት ካደረጉት የአፋር ሕዝብ የፖለቲካ ድርጅቶች የአፋር አብዮታዊ ዴመክራሲያዊ አንድነት ግንባር አንዱ ነው። የድርጅቱ ሊቀመንበር አቶ ማህሙድ ጋአስም በአውሮፖና በአሜሪካ እየተዘዋወሩ የአፋር ሕዝብ ከተቀሩት ኢትዮጵያውያን

[161] <u>ክብሪት</u> የካቲት 7 ቀን 1994